# አ ዳ ፍ ኔ

# ፍርሃትና መክሸፍ

መስፍን ወልደ ማርያም

2007 ዓ.ም.

© መስፍን ወልደ ማርያም
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ISBN 978-3944-854-5-1

አዲስ አበባ
2007

አዳፍኔ ፍርሃትና መክሸፍ

# ሐውልት



ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ

## ዋጋቸውን ላላገኙ

## ለኢትዮጵያ አርበኞች

የፋሺስት ኢጣልያን ወረራ ለመቋቋም በእንግሊዝ አገርና በአውሮፓ በሙሉ የተደረገውን የፖሊቲካ ትግል የነጭ ዘረኛነትን አጥሮች ሁሉ ተሻግረው ሰው በመሆን በፈታውራሪነት ለመሩት

## ለወይዘር ሲልቪያ ፓንክኽርስት

የዜግነት ግዴታቸውን በአውሮፓ በተለያዩ መንገዶች ለፈጸሙ

## ለጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ
## ለአብዲሳ አጋና ለዘርዓይ ደረስ

የሁሉንም ውለታ በአክብሮት እያስታወስሁ ለሚቀጥለው ትውልድ አስተላልፋለሁ
ሰዳውን የሚከፍል ትውልድ ስስቲጠጣ እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈላቸው

## ማውጫ


ቁም ነገሩ ....... 8

የአገር መኖር ወይም አለመኖር....... 8

**ምዕራፍ ፩ _መግቢያ ....... 19**

የትምህርት ማኅበረሰባዊ ዓላማ ....... 19
ከመሀይምነት የወጡ አንባቢዎች ....... 23
ለምን አስደነገጠ? የእኔ የኢትዮጵያ ታሪክ ግንዛቤ....... 28
የለውጥ እንቅስቃሴዎች ....... 39
ማኅደረ ሥልጣን ወይም የፖሊቲካ ቤት ....... 41
ደርግና ወያኔ ....... 42

**ምዕራፍ ፪ መቅድም ....... 43**

ከወላጆቻችን የተረከብነው....... 43
የቅርብ ታሪካችን....... 45
የመክሸፍ ባህል ....... 49
ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ....... 53

**ምዕራፍ ፫ _አዳፍኔና መክሸፍ ....... 58**

መክሸፍና አዳፍኔ ....... 58
አዳፍኔ የመክሸፍ ወላጅ አባት....... 62
ትምህርትና ማኅበረሰብ....... 63
ትምህርትና ለውጥ ....... 66
ትምህርትና ውጤቱ....... 69
ትምህርትና ኀሠኛነት....... 70

**ምዕራፍ ፬ የመክሸፍ መሠረት....... 72**

መነሻ ....... 72
የመክሸፍ ምንጭ ....... 73
ትናንትን አለማስታወስ....... 89
ነገን አለማሰብ....... 96

**ምዕራፍ ፭ የታሪክ ጉዞ ....... 97**

ነጻነት፣ እውነት፣ እውቀት፣ እድገት ....... 97







ታሪክ ምንድን ነው? ....... 98
የትውልዶች መወራረስ ....... 99
የታሪክ መሠረት ....... 105
*የተፈጥሮ ታሪክ*....... 106
የሰው ልጆች ታሪክና ችግር ....... 107
ጥያቄ:-- የውጭ ሰዎችና ታሪካችን ....... 116

**ምዕራፍ ፮ የኢትዮጵያ ህልውናና አርበኝነት....... 121**

መሬትና ህልውና ....... 121
ህልውናና የአርበኝነት ተጋድሎ....... 123
የፋሺስት ኢጣልያ ወረራና የኢትዮጵያ አርበኞች....... 126
የአርበኞቹ ተጋድሎ ያስገኘው ክብር....... 132
የላዩ ታች፣ የታቹ ላይ ....... 134
የውርደት አፋፍ ....... 141

**ምዕራፍ ፯ _የኢትዮጵያ ህልውና፡ ባንዳነትና ሰደተኛነት ....... 146**

ስደተኝነት....... 146
ባንዳነት ወይም ለኢጣልያ መገበር ....... 149
ባንዳነት በኢጣልያ ዘመን ....... 155
ባንዳነት በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን....... 161

**ምዕራፍ ፰ _በመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የቀረቡ ትችቶች....... 165**

ትችት አንድ የማዕርጉ በዛብህ ትችት....... 165
ትችት ሁለት ከሸሬት እና እውነት አኩያ እና መንትያ ሲኾኑ . . . ....... 175
ትችት አራት በታምራት ነገራ....... 185

**ምዕራፍ ፱ የትችቶች ትችት ....... 209**

መግቢያ ....... 209
***አንድ በማዕርጉ በዛብህ ትችት ላይ***....... 211
*ሁለት በታምራት ነገራ ሐተታ ላይ*....... 214
***ሦስት በክፍሉ ትችት ላይ***....... 221
አራት በዳንኤል ክብረት ትችት ላይ ....... 222
አምስት በዳንኤል ጭፍሮች ትችት ላይ ....... 225
እነሰ አቤ አምግዕዝየ ዞሉ ሰብእ ሐሳዊ ውእቱ! ....... 225
ፍሬ-አልባ ጩኸት ....... 225
መስፍን ወልደ ማርያም የካቲት 2005....... 225
ስድስት በብርሃኑ ደቦጭ ትችት ላይ ....... 230
*ሰባት በማስረሻ ማሞ ትችት ላይ*.......ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.
የሌሎች ሰዎች ትችቶች....... 237

**ምዕራፍ ፲ መደምደሚያ ............................................................ 239**

ምኞት ክልክል ነው ............................................................ 239
አዳፍኔና የፍርሃት ሰንሰለቱ ............................................................ 244
ትምህርትና እውቀት ............................................................ 249
የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ............................................................ 252
እውቀትና ሥልጣን ሲታገሉ ............................................................ 255
መርዘኛው ትውልድና ቅብብሎቹ ............................................................ 258
ጅብ መጥራት ............................................................ 264






# ምስጋና


ብዙ ሰዎች ረድተውኛል፤ ዘመኑ ሰዎችን ማመስገን እንደመወንጀል የሚቆጠርበት በመሆኑ ስማቸውን አልጠራም፤ በደፈናው ግን በበተለየዩ መንገዶች የረዱኝን ወዳጆች በጣም አመሰግናለሁ፤ በተለይም ለሁለት ሰዎች ባለዕዳቸው መሆኔን መግለጽ ግዴታዬ ነው፤ ትጋታቸው ስንፍናዬን፣ ጥንካሬአቸው ድካሜን፣ እውቀታቸው አለማወቄን እየሸፈነ ሥራው እንዲያልቅ አድርገዋል፤ ከነሱ ጋርም በስተጀርባ ሆነው በጥበብ ችሎታቸው በሙሉ ልብ ያገዙኝን ሰዎችም በጣም አመሰግናለሁ፤ ሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ በተለያዩ መንገዶች የረዱኝን ሰዎች ፍሬው ቢጎመዝዛቸውም በጸጋ እንዲቀበሉት ከውለታ ጋር አሳስባዋለሁ፤ በመጨረሻም በሩቅም ቢሆን ያለመሰልቸት በብዙ ነገሮች የረዳችኝን ልጄን ዶር. መቅደሰ-ታሪክ መስፍንን በጣም አመሰግናለሁ፤ እግዚአብሔር ለሁሉም ረዳት ይስጣቸው፡፡

መስፍን ወልደ ማርያም
ግንቦት 2007 ዓ.ም.

# ቁም ነገሩ
# የአገር መኖር ወይም አለመኖር

የአገርን ህልውና ለመጠበቅ ከጠላት መከላከል ዋና ሥራ ሆኖ ሌላ ሥራ ሁሉ ተዘንግቶ፣ ወይም ትኩረት ሳይሰጠው ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኋላ-ቀር ሆነ፤ የአገርን ህልውና መጠበቁ የነገሥታቱና የሕዝቡ ዋና ተግባር ሆኖ ምዕተ-ዓመታት ተቆጠሩ፤ ሕዝቡ ህልውናን የሚጠብቀውን ጀግንነትና አርበኝነት እያወደሰና እያሞገሰ፣ እየሸለመና እያከበረ መኖርን ባህሉ አደረገ፤ ይህ ባህል ጀግንነትና አርበኝነትን ማክበር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብም እርስበርሱ የሚመዛዘንበትና የሚከባበርበት መለኪያ ሆኖት ቆየ፤ ትዳርም ሆነ ንብረት፣ ተሰሚነትም ሆነ የኃላፊነት ክብር መፍለቂያ ጀግንነትና አርበኝነት ነበሩ።



በዝብዝ ካሣ ቴዎድሮስን ሊወጋ የመጣውን የእንግሊዝን ጦር ሲቀበሉ

በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ-ዓመት ግን በኋላ አጼ ዮሐንስ የሆኑት አባ በዝብዝ ካሣ ይህንን የቆየውን የህልውና ሕግ ሽረውታል፤ አንድ ጊዜ አይደለም ሁለት ጊዜ፤ መጀመሪያ አጼ ቴዎድሮስን






ሊወጋ የሚጓዘውን የእንግሊዝ ጦር ግዛታቸውን አቋርጦ ወደመቅደላ ሲጓዝ እያስተናገዱና መንገድ እየመሩ የአገርንና የሕዝብን ህልውና ደረጃ ዝቅ አድርገው የራሳቸውን የሥልጣን ጥም፣ ወይም የቴዎድሮስ ሎሌ በነበሩበት ጊዜ የተመኙትን ሹመት ባለማግኘታቸው ቂም ይዘው ይሆናል፤ በዝብዝ ካሣ ከአገር ህልውና ይልቅ ቅድሚያ የሰጡት ለሥልጣን እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው፤ እንዲጋጣሚ ሆኖ የእንግሊዞች ዓላማ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሳይሆን በአጼ ቴዎድሮስ ላይ ብቻ የተቃጣ ስለነበረ ኢትዮጵያ ተረፈች።



በዝብዝ ካሣ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ የዘመተውን የእንግሊዝ ጦር መሪዎች ሲጋብዙ



በዝብዝ ካሣ መቅደላን ለብሮ የሚመለሰውን የእንግሊዝ ጦር ሲሸኙ[1]

በዝብዝ ካሣ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑም በኋላ ለእንግሊዞች ያደረባቸውን የውለታ ተገዢነት የግል አድርገው በመያዛቸውም ይሁን ወይም በመፍራት ኢጣልያንንና እንግሊዝን ላለማስቀየም መጣራቸው በብዙ መንገድ ይታያል፤ በዚህም ምክንያት ለሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የብረት አጥር ሆነው የቆዩትን ጀግና፣ ራስ አሉላ አባ ነጋን ገሸሽ በማድረጋቸው የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል በር ለኢጣልያኖች ከፍተዋል፤ ራሳቸው ለእንግሊዝዋ ንግሥት በጻፉት ደብዳቤ ገና በጠዋቱ በ1872 ግልጽ አድርገውታል፤ በእንግሊዝ አጋዥነት የሰሜኑን በር ለኢጣልያ ከፈቱ።

[1] ስዕሎቹ በዘመኑ በወጡ ILLUSTRATED LONDON NEWS በሚል መጽሔት የታተሙ ናቸው።





አጼ ቴዎድሮስ ሞተው፡--

መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ፤
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ፤

ተብሎ ከተለቀሰ በኋላ በዝብዝ ካሣ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነውም ከእንግሊዞች የመንፈስ ጥገኝነት እንዳልወጡ ራሳቸው ለእንግሊዝዋ ንግሥት በጻፉት ደብዳቤ ያረጋግጣሉ፡--

... ጥንቱንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመንግሥት የበቃሁ እርስዎ በሰጡኝ መድፍ፣ ነፍጥ፣ ባሩድ ነው፤[2]

ቢሆን ኖሮ በሚል አስተሳሰብ ታሪክ አይነገርም፤ ቢሆን ኖር ማለት የሚቻል ቢሆን አሉላ አባ ነጋ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቢሆኑ ኖሮ የሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ታሪክ፣ በተለይም የኢጣልያ ታሪክ ምናልባት የተለየ ሊሆን ይችል ነበር፤ ራስ አሉላ በዶጋሊ ጦርነት ላይ አምስት መቶ ያህል የኢጣልያ ወታደሮችን (ነጮች) ተጋፍጠው ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር ወራሪውን መልሰውት ነበር፤ ከዚህ ለመማር ያልቻለውን ጠላት ደጋግመው ለመቅጣት ዝግጁ ነበሩ፤ ተናግረዋልም፤ ነገር ግን በዶጋሊ ጦርነት በኢጣልያኖች ላይ የደረሰውን ጉዳት እንግሊዞችን ጨምሮ አውሮፓውያንን ስላስቆጣ ራስ አሉላን ጨፍጫፊ፣ አረመኔ እያሉ ስም ሲሰጧቸው አጼ ዮሐንስ ከአውሮፓውያን ጋር መስለፋቸው የሚያሳዝን ነው፤ ራስ አሉላን ለአውሮፓውያን አጋልጠው ከመስጠታቸው በተጨማሪ ሥልጣናቸውንም መገደባቸው የኢትዮጵያን ሀልውና ለአደጋ አጋልጧል፤ ለኢጣልያ በሩን ከፍቷል።

የተጠቀሰው የአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ የተጻፈው አሥራ ስድስት ዓመት ያህል ከአድዋ ጦርነት በፊት ነው! በዚያን ጊዜ

[2] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፣

የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሚያገባቸው ነገር አልነበረም።

በዶጋሊ ጦርነት ላይ ራስ አሉላ ያገኙት ሙሉ ድል አጼ ዮሐንስን አላስደሰተም፤ ከውጭ ምንጮች የተገኘው መረጃ ‹‹በዚያ (በዶጋሊ) ጦርነት እንድትከፍት ማን ፈቀደልህ? ወታደሮቹስ ያንተ አይደሉም፤ የኔ ናቸው፤ ቀኝ እጅህን እቆርጠዋለሁ!›› ብለው ቁጣቸውን መግለጻቸው ተመዝግቧል፤[3] ራስ አሉላ በቁጣ ፖርታል ለሚባለው የእንግሊዝ መልክተኛ የሚከተለውን ብለውታል፡--

**‹‹ኢጣልያኖች ወደሰሀጢ እንዲመጡ የምፈቅድላቸው እኔ የሮማ ገዢ ስሆን ነው፤ በፊት አንድ ጊዜ አሸንፌአቸዋለሁ፤ ከገፉ እንደገና እመታቸዋለሁ።[4]**

ራስ አሉላና ፖርታል የተገናኙት እኤአ በ1887 ነው፤ የኢጣልያ ጦር ወደዶጋው ሲገፋ ራስ አሉላና ንጉሥ ሚካኤል ኢጣልያኖቹን ለማቆም ቢመክሩም አጼ ዮሐንስ ፊታቸውን ወደምዕራብ አዙረው ሄዱ፤ ስለዚህ ሁኔታ ሀጋይ ኤርሊክ ሲደመድም

**ዮሐንስ አሉላን ከሻሩ በኋላ ስለመረብ-ምላሽ ምንም ዓይነት መከላከያ ሳያደርጉ ቀሩ፤ እንዲያውም ደበብን (የኢጣልያኖች አገልጋይ የነበረ) የአከለ ጉዛይ ገዢ አደረጉ፤ አሉላን ከአስመራ ማስነሣት ትልቅ ስሕተት እንደነበረ ወዲያው ታወቀ፤ ይህ ድርጊት ያለምንም ጥርጥር ኢጣልያኖች በኋላ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ እንዲህ ዋና ተዋናይ እንዲሆኑ ያስቻላቸው ነው።[5]**

---

[3] Haggaai Erlich, Ethiopia and Eritrea During the Scramble for Africa: A Political Biography of Ras Alula, 1875-1897, African Studies Center , Michigan State University, East Lansing, 1982, p. 110.

[4] እዚያው ገ. 115.

[5] እዚያው ገ. 122.





ሀጋይ ኤርሊክ በራሱ ድምዳሜ የመረብ ምላሽን ከኢትዮጵያ መነጠል የአጼ ዮሐንስ ስሕተት መሆኑን ከገለጸ በኋላ አዘነላቸውና የሚከተለውን ይጽፋል፤--

**ኤርትራን (አሁን ኤርትራ ይላል፤ ኤርትራ ግን ገና አልተፈጠረችም፤) ለማጣት ኃላፊነቱ የሳቸው ብቻ አልነበረም፤ ኢትዮጵያን ከመረብ ማዶ ያለውን ግዛት ያሳጣት በዋናነት የአጼ ዮሐንስ ታማኝ የጦር መሪያቸው አመራር ነው፤ የመረብ ምላሽ ግዛታቸውን ለመጠበቅ ራስ አሉላ ከሦስት ኃይሎች ጋር መቋቋም ነበረባቸው፤ በምኞት የተወጠረው አውሮፓዊ ጎረቤት (ኢጣልያ)፣ ያልተከለለ ወሰን፣ ዋና ከተማቸውን የንግድ ማእከል ለማድረግ የነበራቸው ፍላጎት ...[6]**

አስተሳሰቡ የተምታታበት ቢመስልም ያው አውሮፓውያን ሁሉ እሪ! ያሉበትን የዶጋሊን ጦርነት በልቡ ይዞ ነው፤ በፍሬ ነገሩ ላይ እውነቱን ፍርጥ አድርጎ ገልጾ ወደመጨረሻው ላይ ይበራርዘዋል፤ ለኢጣልያ መስፋፋት አጼ ዮሐንስ ‹‹ትልቅ›› ስሕተት ፈጽመዋል ያለውን መለስ አድርጎ ስሕተቱ የሳቸው ብቻ ሳይሆን የራስ አሉላም ነው ይላል፤ የመጨረሻ ኃላፊነት የሚያርፈው አጼ ዮሐንስ ላይ ነው፤ ንጉሠ ነገሥት ነበሩና! ለማናቸውም ምስክራችን ሀጋይ ብቻ አይደለም፤ አቶ ተክለ ጻድቅም የሚከተለውን ይላሉ፡--

**ከዶጋሊው ጦርነት ወዲህ የጦር ጠቅላይ አዛዥነቱን ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ አሉላ አንሥተው ለታላቅ ወንድማቸው ልጅ ለራስ ኃይለ ማርያም ሰጥተው አሉላን በሐማሴን ግዛት ስለወሰኗቸው ቅሬታ ነበራቸው ይባላል።[7]**

---

[6] እዚያው ገ.122

[7] አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፤ አዲስ አበባ፤ ገ.470.

አሉላም ከተሻሩ በኋላ ኢጣልያኖች የዶጋሊን ወድቀት ለመሸፈን አዲስ ጦርነት ለመክፈት እየተዘጋጁ መሆኑንና 20000 ወታደሮች ሰሀጢ ላይ መመሸጉ በመሰማቱ ወደዚያ ለመዝመት በሚዘጋጁበት ጊዜ መኳንንቶቻቸው ወደንጉሠ ነገሥቱ ገብተው

**ጃንሆይ ሁላችንም እስከምጥዋ ወርደን ኢጣልያኖችን ከእናታችን ከኢትዮጵያ ምድር እንድናስወጣቸው ይፍቀዱልን አሏቸው::[8]**

ይህ የመኳንንቱ ጥያቄ በጉዳዩ አጼ ዮሐንስ እንዳላሰቡበት የሚያመለክት ይመስላል፤ ከዚህ ጋር አያይዘውም አጼ ዮሐንስ

***ሀገሬ ሆይ ስማ! መኳንንቶቼ፣ ወታደሮቼ፣ ሕዝቦቼ ስሙ! በመጋቢት 25 ቀን በምጥዋ መንገድ አቅንተህ ለጦርነት እንድትገሰግስ የኢትዮጵያ መንግሥት በጽኑ ያዝሃል፤ ወደፊት ገስግስ እንጂ ወደኋላ አትቅር።***

ይህ የጦርነት አዋጅ ነው፤ በዚሁ መሠረት ከሰማንያ እስከመቶ ሺህ የሚገመት ጦር ይዘው አይለት ደርሰው የኢጣልያኖች ጦር ‹‹በጥንካሬ›› መመሸጉን ሲረዱ ‹‹በከንቱ ሕዝብ ማስጨረስ ይሆናል›› በሚል ስጋት ሲያመነቱ ኢጣልያኖች አዲስ ነገር ይዘው ብቅ አሉ፡--

**‹‹በአየር ላይ እየተወረወረ የሚጮህ የኤሌክትሪክ መብራትና እንደትልቅ ኳስ በሰማይ ላይ የሚያንዣብብ ... (ነገር) ወደሰማይ ከመወርወር ጋር ባቡሮችንም በማስጮህ ለማስደንበር ከፍ ያለ ሙከራ አደረጉ፤ እውነትም ወታደሩ በዚያን ጊዜ የኤሌክትሪክ መብረቅ አይቶ ስለማያውቅ መብረቅ ከሰማይ ወርዶ የሚመታው መስሎት ሸሽት ዠምሮ ነበር ይባላል።**

[8] እዚያው ገ. 470.





**አጼ ዮሐንስና መሪዎቻቸው የድንጋጤ መልክ ሳያሳዩ ወታደሩን በማረጋጋት ለጦርነት ቢዘጋጁም ጣልያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ጦርነት የማይዠምሩ ሆነ፤ ስለዚህ አንድ ወር ጠብቀው ንጉሠ ነገሥቱ ወደአሥመራ ከዚያም ወደመቀሌ ከመመለሳቸው በፊት ከኢጣልያ ጦር ሠራዊት አዛዥ ከጄኔራል ሳን ማርሳኖ ጋር የሰላም ድርድር ይሞክሩ ዠመር::[9]**

ልብ ልንል የሚገባው ጊዜውን ነው፤ ከላይ የተዘረዘረው ሁሉ የሆነው በ1880 ዓ.ም. ወይም ከዚያ በፊት ነው፤ አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት በ1882 ዓ.ም. ነው፤ እንግዲህ የሰሜኑ ምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል በኢጣልያ ስር ለመውደቁ አጼ ምኒልክን ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? አጼ ምኒልክ በውጫሌ ውል የሠሩትን ስሐተት በአድዋ ላይ አርመውታል፤ አጼ ዮሐንስ ከእንግሊዞች ጋር ባደረጉት ውል የተሠራውን ስሕተት ማረም አልቻሉም::

የአገርንና የወገንን ህልውና በሥልጣንና በሹመት መለወጥ ልማድ ሆነና በሃያኛው ምዕተ-ዓመት የኢጣልያ ወረራም ጊዜ በብዙዎች ላይ ታየ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሸሽተው ወደእንግሊዝ አገር ሄዱ፤ በሰሜን ራስ ሥዩም፣ ራስ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳና ሌሎችም፣ በመሀል አገር እነራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ እነራስ ጌታቸው አባተ፣ ሌሎችም ለኢጣልያ ገበሩ::

በሃያኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ፣ በተለይም ከአልጋ ወራሽ ንጉሥ ተፈሪ ጀምሮ ቀስ በቀስ የጀግንነትና የአርበኝነት ሚዛኖች ወይም መለኪያዎች እየተለወጡ ንግድና ገንዘብ፣ ተንኮልና ሴራ ሚዛን የሚደፉ ሆኑ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞም የአገርን ህልውና መጠበቅና የወገንን ክብር አለማስደፈር ለንግድና ለገንዘብ፣ ለተንኮልና ለሴራ የክብር ቦታቸውን ለቀቁ፤ ማኅበራዊ ኃላፊነት ተሻረና የግል ጥቅምን ማሳደድ ባህል እየሆነ መጣ፤ ጌታ ከሎሌዎቹ ጋር መብላት ቀረ፤ ሁሉም በከተማ፣ በየቤቱ ተከተተ፤ የራስ ካማ ሰፈር፣ የደጃች ወልደ ጻድቅ ሰፈር፣ የራስ ደስታ ሰፈር፣

[9] እዚያው ገ. 472-473.

የቢትወደድ ወልደ ገብርኤል ሰፈር፣ የራስ ሙሉጌታ ሰፈር፣ የፊታውራሪ ሀብተ ጊርጊስ ሰፈር ... ቀስ በቀስ እየሳሳ ተራቆተ፤ ጌትነትና ደሀነት የግል ሆኑ፤ ጌትነትና ደሀነት ራቁታቸውን አደባባይ ወጡና ሁሉንም አጋለጡት፤ ጌታው በሩን ዘግቶ ይበላ ጀመረ፤ ደሀው ከደጅ ጥናት ወደልመና ተሸጋገረ፤ ።

የኢጣልያ ወረራ በበኩሉ አዲስ ስያሜዎችን አመጣ፤ ፒያሳ፣ መርካቶ! ደርግ የራሱን ማኅተም ፈለገ፣ ስምን መልእክ ያወጣዋል እንደሚባለው በዜሮ ገባው፤ 01፣ 02፣ 03፣ ፡፡፡ ወያኔ ሁሉንም አፈራርሶ የራሱን ማኅተም ለማኖር ቡልቡላ፣ ሳሪስ፣ ሰሚት፣ ገርጂ፤ ጀሞ ...

በተለይም ከኢጣልያን ወረራ በኋላ ንግድና ገንዘብ፣ ተንኮልና ሴራ ባህል እየሆነና እየጠነከረ ሄደ፤ እየተከተፈና እየተመነዘረ አገር ከሚለው ስፋት ጋር የሚቆም ሰው ክወገን ውስጥ ጠፋ፤ ወገን ማለት ገንዘብ ሆነ፤ የራሳችንን አማልክት እየሻርን ለሌሎች አማልክት እንሰግዳለን፤ የራሳችንን ጻድቃንና ሰማዕታት ንቀን የተዋስናቸውን እያደነቅን እናከብራለን፤ የራሳችንን አእምሮ ፈረካክሰን አስተኝተን የሌሎችን አእምሮ እንበደራለን፤ የራሳችንን ድንቁርና ማሸነፍ ሳንችል በሌሎች ድንቁርና እናጌጣለን፤ ባዶ መሆናችንን ሳናውቅ ያቀረሸናል፤ እየተራብን እንደነፋለን፤ እየተጠማን እንሰክራለን፤ እየተረገጥን እናጨበጭባለን፤ እየተቀማን እንዘፍናለን፤ እየጫጨን እንቀኛለን፤ ስለዚህም ኢትዮጵያ የድንኮች አገር ሆነች፤ የአገርና የወገን ፍቅር ተሻረ፤ እኛነታችንን፣ ማንነታችንን የሚያስተምሩን ገንዘብ ያላቸው የውጭ ሰዎች ሆኑ፤ ራሳችንን ጠላን፤ አገራችንን ጠላን፤ ስደትን ወደድን፤ በዓለም በሙሉ፣ በየአህጉሩ፣ በየአገሩ መከራ በልተን ተሰራጨን፤ ረከስን፤ ተዋረድን፤ አባቶቻችንንና እናቶቻችንን አዋረድን፤ በያለበት ብዙ ዓይነት ስሞች ወጡልን፤ እኛ በሥራችን እንዋረድ፤ አባቶቻችንና እናቶቻችን በሕይወታቸው ያስከበሩትን ኩራትና ክብር እንዴት እናስገፍፋለን?

ችግሩ የውርደት ብቻ ሆኖ አያበቃም፤ የህልውና ስጋትም እያስከተለ ነው፤ አባቶቻችንና እናቶቻችን በሕይወታቸው ያስረከቡንን ኩራትና ክብር የተጎናጸፈ ህልውና በውርደት





ከለወጥነው፣ ነፍሳችንን በገንዘብ የምንሸጥ ከሆነ፣ የአገራችን ባለቤቶች መሆን አቅቶን በየሰው አገሩ መናኛ አገልጋዮች መሆንን ከመረጥን፣ የእናቶቻችንንና የአባቶቻችንን አገር ለሌሎች በርካሽ አከራይተን፣ በአገሩ የቀረውንም መሄጃ ያጣ ደሀ በተፈለገበት የእሳት ራት ሆኖ እንዲያገለግል የምናከራይ ከሆነ ኢትዮጵያዊነታችን በአባቶቻችንና በእናቶቻችን የሕይወት መስዋእትነት ላይ የተገነባ መሆኑን አውቀን አፍርሰነዋል ማለት ነው፤ የአባት-የእናት ቃል-ኪዳንን ኢትዮጵያዊነትን አፍርሰን ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሰው ሆነን እንቀጥላለን?

በደርግ ዘመን ተራማጅ ነን ባዮቹ ዓለም-አቀፍ ወዛደርነት እንጂ ብሔራዊ ስሜት የሚባል ነገር የለም ይሉን ነበር፤ ነገሩ ሲሉ ሰምታ የሚባለው ዓይነት ነው፤ በእንግሊዝኛ ዓለም-አቀፍ ወዛደራዊነት proliterian internationalism ነው፤ የተሰካው ‹‹ናሽናሊዝም›› ብሔራዊ ስሜትን የሚገልጽ ነው፤ የተባበሩ ብሔራዊ ስሜቶችን የሚገልጽ ነው፤ ስለዚህም ዓለማቀፍ ወዛደራዊነት ከብሔራዊ ስሜት የሚመነጭ እንጂ የሚጻረር መሆን አልነበረበትም፤ ጥራዝ-ነጠቆቹ ግን ይህ አልገባቸውም።

እዚህ ላይ ቆም እንበልና የተከታታይ ትውልዶቹን የአስተሳሰብ ችሎታ እንመልከተው፤ መጀመሪያ ላይ የፖሊቲካ እምነታቸውን ከብሔራዊ ስሜት አሳልፈው አስተሳሰባቸውን በጣም ሰፊ አድርገው በዓለም-አቀፋዊ ወዛደርነት ላይ የመሠረቱት ሰዎች አንድ ትውልድ ሳያልፍ የፖሊቲካ እምነታቸው ቀኝ-ኋላ ዙር ብሎ ጠበበና ከዓለም-አቀፍ ወዛደራዊነት ወደጎሠኛነት ተለወጠ! ለእኔ ጥያቄው ዓለም-አቀፍ ወዛደራዊነት ጥሩ ወይም መጥፎ ሀሳብ፣ ጎሠኛነት ጥሩ ወይም መጥፎ ሀሳብ መሆኑ አይደለም፤ ለእኔ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ወደዓለም-አቀፋዊ ወዛደርነት የመራውን አስተሳሰብ በአንድ በኩል፣ ወደጎሠኛነት የመራውን አስተሳሰብ በሌላ በኩል ስንመለከተው አለማሰብን የሚያመለክት መዋዠቅ መሆኑ ላይ ነው።

ዓለም-አቀፍ ወዛደራዊነትንና ጎሠኛነትን የማነሣቸው በኢትዮጵያ ሁለቱም የፖሊቲካ እምነቶች የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ሕዝብን ህልውና የተፈታተኑና የሚፈታተኑ

በመሆናቸው ነው፤ እግረ-መንገዴንም ለአርባ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ሕገ-ጎልዮት ገና በተማሩትም ሰዎች አእምሮ እንዳልሰረጸ ለማሳየት ነው፤ በሕገ-ጎልዮት እየተመራን መከራከር ከአቅም ውጭ እስከሆነ ድረስ በቅን መንፈስ ተነጋግረንና ተከራክረን መረታታት አንችልም፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ ተባብረን ፍሬያማ ሥራ ማስመዝገብ የምንችል አይመስለኝም።

ከእውነት የመነጨ እውቀት ላይ ቆመን የትናንቱን መልክ በትክክልና በዝርዝር ከተረዳን ነገን ለማነጽና ለመገንባት አያስቸግረንም።





# ምዕራፍ ፩
# መግቢያ

## የትምህርት ማኅበረሰባዊ ዓላማ

ዱሮ በልጅነቴ የኢጣልያ ወረራ ማብቂያው ላይ የሰው ሁሉ ወሬ ነጻነት እንደነበረ አስታውሳለሁ፤ ዘፈኑ ስለነጻነትና ስለአርበኞች፣ ስለድል አድራጊው ንጉሠ ነገሥት ነበር፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚወራው የመረረ ቁጭት ነበር፤ በኢጣልያና በእኛ መሀከል የነበረውና አሁንም ያለው የእውቀት ልዩነት ለጥቃትና ለውርደት እንደዳረገን በደንብ መረዳታችን ክፉኛ ይቆረቁረን ነበር፤ ስለዚህም ድንቁርናችንን አራግፈን በእውቀት እንድንታጠቅ ዓየሩ በሙሉ የሚያበረታታ ነበረ፤ ትምህርት፣ ትምህርት፣ ትምህርት፣ … እውቀት፣ እውቀት፣ እውቀት!

ፊደል ከቆጠርንበት ከአለቃ ታምራት የመንገድ ላይ ተማሪ ቤት አንድ ጄኔራል መውጣቱን አውቃለሁ፤ ጄኔራል ከፈለኝ ያብዛ፤ አንድ በኋላ ጠበቃ የሆነ ከቅኔ ትምህርት ቤት የተመረቀም አሰፋን የሚባል ጓደኛ ነበረኝ፤ እንግሊዝኛ ፊደል ከቆጠርሁበት ከቀስቋም ተማሪ ቤትም እነዶር. መኮንን ወልደ አምላክና እነንዋይ ገብረ ጻድቅ፣ ሌሎችም ወጥተዋል፤ ቆይቶ ከተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት በተለያዩ መስኮች እስከከፍተኛ የእውቀት ደረጃ የደረሱ ብዙ ናቸው።

በዚያን ጊዜ ማንም ልጅ ቢጠየቅ መልሱ አንድ ነበር:--- ተምሬ አገሬን እረዳለሁ! በዚያን ጊዜ፣ እኔ ልጅ ሆኜ ‹‹ትምህርት ለእንጀራ›› የሚባል ነገር ማንም አያውቅም ነበር፤ እንደምገምተው በዚያን ዘመን ከዛሬው የበለጠ እኩልነት ነበር፤ በደሀዎችና ሀብታሞች በሚባሉት መሀከል ሩቅ የሆነ ልዩነት አልነበረም፤

በኑሮም ሆነ በአስተሳሰብ የሚቀራረቡ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ነበሩ፤ ዛሬ የሚታየው ዓይነት ልዩነት አልነበረም፤ የደሀ ቤትና የሀብታም ቤት አይመሳሰሉም፤ የደሀና የሀብታም ምግብ አይመሳሰሉም፤ የደሀና የሀብታም ልብስ አይመሳሰሉም፤ዛሬ ሀብታምና ደሀ አይጠራሩም፤ ቢጠራሩም አይደማመጡም፤ በጠብ እስቲገናኙ ድረስ እየጠበቁ በፍቅር አይገናኙም፤ የመቀሌ ነዋሪዎች ለሀብታሞቹ መንደር የሰጡት ስም ‹‹አፓርቴይድ›› የጊዜውን ሁኔታ የሚገልጸው ነው፤ ኢትዮጵያ የዜጎች አገር ከመሆን ይልቅ ያላቸውና የሌላቸው መኖሪያ፣ ያውም የግዴታ መኖሪያ እየሆነች ነው፤ ወጣቶች በኢትዮጵያ ከመኖር ለመዳን የማይመርጡት አደጋ የለም።

አዳፍኔ ነጻነትን አከሸፈ፤ እኩልነትን አከሸፈ፤ ትምህርትንና እውቀትን ከማኅበራዊ ዓላማ ወደግለሰባዊ ዓላማ ለወጠ፤ ወይም ግለሰቡን ከማኅበረሰቡ አስወጣው፤ ማኅበረሰቡ ባዶ ቀፎ ሆነ፤ የንቦቹ ንግሥት አዳፍኔ ሆነች፤ ኢትዮጵያ የአገዛዙ ሹማምንት ቤት ሆናለች፤ ኢትዮጵያ ከቤታቸው የተባረሩና ቤታቸውን በመልቀቅ ላይ ያሉ የዘጠና ሚልዮን ኢትዮጵያውያን እሾህ ሆናለች፤ እሾሁን ከመንቀል ይልቅ ወደእሳት መሸሽ የኢትዮጵያውያን የኑሮ ግዴታ እየሆነ ነው፤ እሾሁን ለመንቀል ከሚከፈለው ማናቸውም ዓይነት ዋጋ እሳት ውስጥ መኖሩ እንደሚጎዳ እያዩም ኢትዮጵያውያን እሳቱን እየመረጡ ነው።

በሕጋዊ ሥርዓት ለሕግ የማይገዙ ሙሉ ሥልጣን ያላቸው ሹሞችና ምንም የሕግ ከለላና መብት የሌላቸው ሰዎች አገራችን ነው በሚሉት ቦታ ባይተዋር የሆኑበት ነው፡

አዳፍኔ ኢትዮጵያ የወሬ አገር እንድትሆን አድርጓታል፤ አንደኛ እውነትን በማፈን፤ ሁለተኛ ትምህርትንና እውቀትን በማፈን፤ ሦስተኛ እውነት የሚሰራጭባቸውን መንገዶች ሁሉ በመዝጋት፤ አራተኛ ውሸትን እያራቡ የሚያሰራጩ አፈ-ጮሌዎችን በሎሌነት በማሳደር፣ አምስተኛ እውቀት በኢትዮጵያ እንዳይስፋፋ፣ መጻሕፍት እንደልብ እንዳይታተሙና በርካሽ እንዳይሰራጩ በማድረግ ኢትዮጵያ የወሬ አገር ሆናለች፤ አዳፍኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ሰንጎ ገዝቷል፤





ስለዚህም የአዳፍኔ አገዛዝ ባህል የሆነውን ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብ ወሬኛ መሆኑም ባህል ሆኗል፤ ብዙ ሰዎች እንደሚናደዱና አካኪ ዘራፍ እንደሚሉ እርግጠኛ ነኝ፤ ይህም ባህል ነው፤ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ነን የሚሉ ከሰሜን እስከደቡብ ኢትዮጵያ የተውጣጡና የተለያዩ ቡድኖች በዓይነ-ደረቅነትና በድንቁርና እርግጠኛነት በመድረክ ላይ እያረገረጉ ለብዙ ዓመታት ውሸትን በአደባባይ ሕዝብን ሲያወናብዱ ከማርክሲስት-ሌኒንስት ፖሊቲካ ጋር አፈር በልተዋል፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውሸት አይሞትም።

ገና የወያኔ ሠራዊት አዲስ አበባ እንደገባ ሁለት ዓይነ-ደረቆችና በድንቁርናቸው የሚተማመኑ ወያኔዎች የታሪክ እውነትን ለማዛባት ራሳቸውን በአስተማሪነት ሾመው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በራስ መኮንን አዳራሽ መምህራኑን ሰበሰቡ፤ **ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል** በሚባለው ባህላዊ መመሪያ መሠረት ለዩኒቨርሲቲው መምህራን የኢትዮጵያን ታሪክ ለማስተማር ደፈሩ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአንድ መቶ ዓመታት እንደማይበልጥ ተናገሩ፤ ዋናው ዓላማቸው ግን የዩኒቨርሲቲውን የእውቀት ሥልጣን ለመግፈፍ፣ በዚያ ውስጥ በእውቀታቸው ተመርጠው የገቡትን መምህራን ለማዋረድ፣ ዩኒቨርሲቲውንና መምህራኑን በማዋረድ እውቀትን ለማዋረድና ጉልበትን ለማንገሥ ነበር፤ ቅል ድንጋይን እንደሚሰብር በተግባር ለማሳየት ነበር።

አንድ የውጭ አገር ጸሐፊ በኢትዮጵያ ውስጥ የታሪክ ማስረጃ የሚባል ነገር ሁሉ ጠፍቶ በጣም ጠጣር በሆነ ድንጋይ ላይ የተጻፈው ብቻ ቀርቷል ይላል፤ በኤርትራም ሆነ በትግራይ፣ ወይም በሌሎች ቦታዎች በድንጋዮች ላይ ተጽፎና ተቀርጾ ስለቀረው ማስረጃ ሲናገር ነው፤ ስለዚህም ድንጋይ ለድንጋይ አይናበብም ወይም አይነጋገርምና ነው እንጂ መረጃው በእጃቸው ነው።

የዩኒቨርሲቲው መምህራን ተቃውሞ አሰሙ፤ ማን ቢሰማ! ቢቸግራቸው ብዙ መምህራን አዳራሹን እየጣሉ መውጣት ጀመሩ፤ ዓይነ-ደረቆቹ ቀጠሉ፤ እንደተናቁ አልገባቸውም፤ እንዴት ብሎ ነው የሚገባቸው? እውነትን ይዘው• ሲጋፈጧቸው በፍርሃት ተርበደበዱና ዱላቸውን አንሥተው ሊያመማር አርባ ዓመታት ያህል

የፈጀባቸውን አርባ ያህል ምሁራን መርጠው ብቃት ይጎድላቸዋል ብለው በደብዳቤ አስወጧቸው፤ ኢትዮጵያ ከሳች፤ ባዶ ቅሎቹ ወፈሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ባህሉ ነውና በአርምሞ ተመለከተ፤ እውቀትን እየነፈጉ ቁልቁለቱን ሲነዱት እሺ ብሎ ተነዳ!

የእውቀት መለኪያቸውንም ለማሳየት ገነት ዘውዴን የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት አደረጉ፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጥሩም ይሁን መጥፎ፣ በጎም ይሁን ክፉ የእውቀትና የአዲስ ሀሳብ መፍለቂያ፣ የክርክርና የሀሳቦች መፋጪያ የነበረው የእውቀት ማእከል በወያኔ ዘመን የሎሌዎች ማሠልጠኛ ጣቢያ ሆነ፤ ማሰብና መናገር ለተከለከሉ ትእዛዝና መመሪያ ማስተላለፊያ ጣቢያ ተደረገ፤ አንዳንዴም ወደሆቴልነት እየተለወጠ ገንዘብ ማስገኛ ሆኗል፤ የሆቴልነቱ ሥራ ፈቃድም የለው፤ የአገር ውስጥ ገቢም አያውቀው፤ እውቀትን ሲገድሉ ሕግም አብሮ መሞቱ የማይቀር ነው።

የዛሬው ትውልድ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዩኒቨርሲቲ ታሪክ አያውቁም፤ በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሃምሳዎቹ በአፍሪካ ውስጥ የሚወዳደረው ዩኒቨርሲቲ አልነበረም፤ በምዕራብ አፍሪካ ከናይጂርያና ከጋና፣ በምሥራቅ አፍሪካ ከኬንያ፣ ከታንዛንያና ከዩጋንዳ ነጻ ትምህርት እየተሰጣቸው ይማሩበት ነበር፤ ሮበርት ኡኮ የሚባለው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ የኬንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበር፤ ጆርጅ ማጎምቤ የሚባለው የታንዛንያ ወጣት በኋላ ብዙ አገሮች፣ በኢትዮጵያም ጭምር አምባሳደር እየሆነ ሠርቷል፤ የኢትዮጵያ ዓየር ኃይልም፣ የኢትዮጵያ ዓየር መንገድም ለብዙ የአፍሪካ አገሮች የዘመናዊ እውቀትና ጥበብ ምንጮች ነበሩ፤ መክሸፍ ባህል በመሆኑ ዛሬ ኢትዮጵያ በሁሉም ነገር ከአብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገሮች በታች ነች፤ ቁልቁል መውረድ ባህል ሲሆንና ሕዝብ እሪ! ሳይል ሳይጮህና ሳያለቅስ ገደል አፋፍ ላይ የደረሰ ይመስለኛል።

ይህንን በምጽፍበት ጊዜ አንድ ሰው በራድዮ ስለአድዋ ድል ይናገራል፤ አያይዞም ሳይቸግረው ማይጨውን አነሣ፤ በሰማይ ባይመጣ! የመርዝ ጢስ ባይረጭብን! ... እያለ የማይሆኑ ነገሮችን ደርድሮ ... ይኸ ሁሉ ባይሆን ማይጨውም እንደአድዋ ይሆን





ነበር! ይባስ ብሎ ቴሌቪዥኑ የ1928 ዓ.ም. የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ጦርነት እያሳየ ትረካው ስለአድዋ ጦርነት ነው፤ በሌላ አነጋገር ምስሉና ትረካው የአርባ ዓመታት ልዩነት በመሀከላቸው ነበረ ማለት ነው፤ በጆሮዬ የሚያስሙኝና በዓይኔ የሚያሳዩኝ የተለያዩ ነገሮች ነበሩ፤ እንዲህ ነው የኢትዮጵያ ታሪክ የሚከሸፈው፤ ከአድዋ እስከማይጨው ያሉትን አርባ ዓመታት እኛ ተኝተን እንዳሳለፍናቸው ኢጣልያኖችም ተኝተው ቢያሳልፉ ኖሮ አያሸንፉንም ነበር ብሎ መናገር አለማሰብ ነው፤ መድረኩ የሚሰጠው ለእንደዚህ ያሉ የአስተሳሰብ ችግር ላለባቸው ሰዎች ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የእውቀትን ጥቅም በደንብ ለመገንዘብ ብዙ አጋጣሚዎች ነበሩት፤ ትልቁና ቁልፉ የእውቀት መንገድ ጽሕፈት ነው፤ ፊደል ነው፤ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት የራሳችን ፊደል ነበረን፤ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት የራሳችን በበሬዎች የማረስ ዘዴ ነበረን፤ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት በአጋሜ፣ በየጁ፣ በኮንሶ የእርከንና የመስኖ ዘዴዎች ነበሩን፤ ለምዕተ-ዓመታት ታላላቅ ሐውልቶችንና ሕንጻዎችን የመሥራት ጥበብ ነበረን፤ ከብዙ ምዕተ-ዓመታት በፊት በሰረገላ እንጠቀም ነበር፤ ለብዙ ዘመናት መፍተልና መሸመን የታወቀ ነበር፤ ይኸ ሁሉ ዘዴ እንደእውቀት በጽሑፍ አልተላለፈም፤ ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ አህያ ከመንዳትና በጎጆ ውስጥ ከመኖር ያልወጣበት መክንያት ምንድን ነው?

በኢትዮጵያ ውስጥ እውቀት ፈላጊ አልነበረውም፤ አሁንም የለውም።

## ከመሀይምነት የወጡ አንባቢዎች

እኔ በትምህርት ቤት በነበርሁበት ዘመን ፊደል መቁጠር፣ ውርድ ንባብ፣ አቡጊዳ፣ መልእክተ ዮሐንስ፤ ... እያልን ዳዊት ላይ እንደርስ ነበር፤ ዛሬ ብዙዎቹ ሰዎች ፊደል ከቆጠሩ በኋላ በአቋራጭ የትኛውንም መጽሐፍ አንብቦ ያለምንም ችግር ትችት ለመጻፍ ልማድ እያደረጉት ነው፤ የኔ ትውልድ እንዲህ ለማድረግ ያፍራል፤ እንኳን የማያውቀውን የሚያውቀውንም

ሳይጠየቅ ለመናገር ያፍራል፤ ዛሬ የማያውቁትን በመቀባጠር አዋቂ መስሎ መታየት የተለመደ ነው፤ እስቲ አንዳንዶቹን ተቺዎች ጠጋ ብለን እንያቸው።

አንደኛ ከተቺዎቹ መሀከል ፊደል የቆጠሩና ማንበብ የሚችሉ፣ የመማር ፍላጎት ያላቸው ሰዎች አሉባቸው፤ እነዚህን ትምህርታችሁን ቀጥሉ፤ ተማሩ ከማለት በተጨማሪ የሚነገራቸው ሊያናድዳቸው ይችል ይሆናልና ብተወው ይሻላል፤ ነገር ግን በዚሁ የችሎታ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች መጽሐፉን የጎሣ ጦርነታቸው ማቀጣጠያ አድርገውታልና ትንሽ መልስ ያስፈልጋል፤ ችግሩ ከፊደል ቆጠራ ያላለፉ በመሆናቸው ልካቸውን አለማወቃቸው ነውና ቆማጣን ቆማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል እንደሚባለው ስለሆነ ገብተው ሲያተራምሱ ዝም ብለን ልናልፋቸው አይገባም፤ በትልቅ የአገር ጉዳይ አለቃዬ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት የነበረው ካሣ ወልደ ማርያም እንዲህ ያለው ጉዳይ መታለፍ እንደሌለበት አስተምሮኛል።

ታሪክን የምኖት ሻሽ ቢያከናንቡት በትንሽ ነፋስ ራቁቱን ይሆናል፤ ድንጋይ ቢጭኑበትም በአንድ ጎርፍ እርቃኑን ይታያል፤ በማናቸውም መልኩ ልዩነቶች ያሉበት ሕዝብ አብሮ በሚኖርበት አገር ሁሉ በሁሉም አህጉሮች የሚናናቁ ከዚያም አልፎ የሚጨቆኑ፣ ከዚያም አልፎ በሕግ ከዜግነት ብቻ ሳይሆን ከሰውነት ደረጃ የሚወጡ ጎሣዎች አሉ፤ በአሜሪካና በደቡብ አፍሪካ የቆዳቸው ቀለም ጥቁር በመሆኑ ብቻ የደረሰባቸውን አበሳ በእኔ ዕድሜ ያሉ ሰዎች ያውቁታል፤ በአንዳንድ ጎሣዎች ላይ በህንድ ሲደርስ የነበረውን ግፍ እናውቃለን፤ የሚያስደስተው ነገር በሃምሳ ዓመታት ውስት፣ ማለት ሁለት ትውልድ ያህል ጊዜ ውስጥ የሕዝብ አመለካከት በጣም በመለወጡ በሦስቱም አገሮች (አሜሪካ፣ ህንድና ደቡብ አፍሪካ) የታየው ለውጥ ደስ የሚል መሆኑ ነው፤ በህንድ አብዛኛዎቹ ህንዳውያን ከሚጠየፏቸው መሀከል አንዱ ፕሬዚደንት ሆነ፤ በአሜሪካና በደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ፕሬዚደንቶች ሆነው ተመረጡ!

እኔ በህንድም፣ በአሜሪካም ተማሪ በነበርሁበት ጊዜ እንዲህ ያለ ነገር አይታለምም ነበር፤ የሰው ልጆች ራሳቸውን ሲለውጡ





ማኅበረሰባቸውንም ይለውጣሉ፤ የሰው ልጅ ተፈጥሮ እንደላስቲክ ነው፤ይሳባል፤ይኮራምታል፤ አንድ ልናስታውሰው የሚገባ ነገር አለ፤ በአሜሪካም ሆነ በህንድ፣ ወይም በደቡብ አፍሪካ ብሪታንያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንዳለበት ነው።[10]

እኛ ወደፊት በመራመድ ፋንታ ወደኋላ ሄደን ለቂማችን በሃያ ሚልዮን ብር ሐውልት እንሠራለን፤ የማኅበረሰቡን ሁለንተናዊና ጠቅላላ መከሸፍ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም አብረን ለመራመድ የማንችል መሆናችንን የሚያመለክት ነው፤ ወደእርቅ ለመምጣት መንፈሳዊ ወኔ የለንም፤መንፈሳዊ አባቶችና ሽማግሌዎች የሉንም፤ በሌላ መንገድ መፍትሔ ለማስገኘት ጀግንነቱ ሸሽቶናል፤ ይህንን መከሸፍ አዝሎ በሰሜንና በደቡብ ሱዳን መሀከል ለመሸምገል የተደረገው ሙከራና ወጤቱ ከምኔውና ለምን እንደከሸፈ ሰምተናል።

መንፈሳዊ ወኔውም፣ ጀግንነቱም የሌላቸው የከሸፉ ቀለሆች በአሜሪካና በአውሮፓ ከጉድጓድ ምሽጋቸው ብቅ ጥልቅ እያሉ አትርሱን የሚሉትን እንርሳቸው፤ በኢትዮጵያ ፋይዳ ያልሠሩ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ፋይዳ አይሠሩም።

ሁለተኛው የአንባቢው ክፍል የተማሩና የተመራመሩ የሚመስላቸው ሰዎች ናቸው፤ ከእነዚህ አብዛኛዎቹ ደግሞ ሌላ በሽታ አለባቸው፤ ፈረንጅ ካላቃናቸው እንደተጣመሙ ይቀራሉ፤ ከዚህ በፊትም በሌላ ሁኔታ ላይ የጠቀስሁት አንድ ምሳሌ አለ፤

[10] No amount of palaver about the largely hypothetical past is a substitute for an an analysis of the oresent, which can be checked by direct experience. (c.h. Waddington )p.35 The totalitarianism, on the other hand, does seem to be inevitable; the whole trend of recent history is towards it . One cannot dismiss the Nazis, Fascists, Communists all together for being, in their different ways, totalitarian; fairly soon we shall all be so, in some way or other. The Totalitarians of to-day have taken, with the wrong foot foremost, a step which we shall have to take to-morrow. P.22

... no society is worth much if its members cannot find something which makes them proud to belong to it. (17)

There will never be any great enthusiasm for belonging to a society which is not going forward. (17)

በሀርቨርድ ዩኒቨርሲቲ ተጋብዤ ለጥቂት ወራት በቆየሁበት ጊዜ አንድ የሰሜን ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያዊውን ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብን ለአሜሪካኖች ለማስተዋወቅ ያጠና ነበር፤ ስለዚህም አንድ ቀን ስለዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ጥናቱን እንዲያቀርብ ፕሮግራም ተይዞለት ስብሰባ ነበረ፤ በመጀመሪያው ላይ ስላልነበርሁ እኔ በምደርስበት ጊዜ የከረረ ክርክር ነበረ፤ ኢትዮጵያዊው ዶክተር ሳይንስ ያረጋገጠውን ሁነት ለውጦ ሰው የሚያስበው በልቡ ነው በማለቱ ከባድ ተቃውሞ ገጠመው፤ አንዳንዶች ይህ አዲስ ግኝት ነው እያሉ ሲያሾበት አይሰማውም ነበር፤ የቃል ትርጉም ስሕተት መሆኑ ገባኝና የዘርዓ ያዕቆብን በግእዝ የተጻፈውን ‹ልቡና› ልብ በማለት ከመተርጎም የመጣ ስሕተት መሆኑን ለማስረዳት ሞከርሁ፤ ሲያልቅ ኢትዮጵያዊው ቅሌቱን ተከናንቦ ሄደ፤ ይህንን ሰው እንግዲህ ከተማሩትና ከተመራመሩት ውስጥ አስገብቼዋለሁ።

ከነዚህ ከሁለት ዓይነት አንባቢዎች ውስጥ እኔ የምጠብቀው ምን ዓይነት አስተያየት ነው? ፊደል ቆጣሪዎቹን በማንበባቸው አመሰግናቸውና ጥያቄዎችን ቢጠይቁ ይበልጥ ይማሩ ነበር እላለሁ፤ የተማሩት ደግሞ ወይ የጎሣ መነጽር ሰክተው ባያነቡት ወይ ስለኢትዮጵያ ያላቸው አስተያየት ከኔ ጋር ያልተስማማበትን ምክንያት ቢያስረዱኝ ያስተምሩኝ ነበር፤ ሁለት ሰዎች ብቻ በሙሉ ቁመታቸው ከሌሎች ሁሉ በላይ ሆነው ታዩኝ፤ ክፍፍል ስናደርግ ሁልጊዜም ቤት የሚያጣብብ አይጠፋም፤ አንዳንዱ በግድ ተገፍቶ አንዱ ክፍል ውስጥ ይገባና አይገጣጠምም።

በሁለቱም ክፍፍሎች ውስጥ የጎሣ መነጽር አድርገው ያነበቡት አሉ፤ በጎሣ መነጽር ያነበቡት መማራቸው ለወጉ ነው፤ ፊደል ብቻ በተማሩትና ተማሩ በተባሉት መሀከል ልዩነት የለም፤ በጎሣ ዓይን ያነበቡት ትግርኛና ኦሮምኛ ተናጋሪዎች እንደሚመስለኝ አንደግለሰብም አላነበቡትም፤ የዚህን ትርጉም ላፍታታው ብል ተሳደብህ ይላሉ፤ ነገር ግን እኔ ስጽፈው የትኛውንም ጎሣ ወክዬ ሳይሆን ኢትዮጵያን በአጠቃላይ እያሰብሁ ነበር፤ ጎሣ ወክዬ ብጽፍ የምደብቅበት ምንም ምክንያት የለኝም።





ያን ጊዜም ሆነ ዛሬ በበኩሌ የጎሣ መነጽር የለኝም፤ ልሳሳት እችላለሁ፤ አስተያየቴ ለአንዳንድ ሰዎች አይጥምም ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን የጎሣ ምንም ነገር በውስጤ የለም፤ ለእኔ በጎሣ ደረጃ ወርዶ ማሰብ ከሰውነት ደረጃ መውጣትና ወደአዘቅት መውረድ ነው፤ እዚያ ተርታ በአካልም በአስተሳሰብም በስሜትም አልገኝም፡

መከሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክን ስጽፍ በኢትዮጵያዊነቴ መንፈስ ተይዤ ነው፤ ይህንን መካድ አልችልም፤ ከሰማይ እንደወረደ ሰው ሆኜ ስለኢትዮጵያ ታሪክ መጻፍ እችላለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ታሪክ ጸሐፊ (ወይም የታሪክ ተመራማሪ) ካለ የሚናገረውን የሚያውቅ አይመስለኝም፤ ከኢትዮጵያዊ ትውልዴ፣ ከኢትዮጵያዊ አስተዳደጌና ስሜቴ፣ ከበርበሬው መፋጀትና ከቡናው ትኩስነት ራሴን ሙሉ በሙሉ አግልዬ ስለኢትዮጵያ መናገር እችላለሁ ብዬ አልዋሽም፤ በእኔ ውስጥ የሰረጸው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ በምድረ ኢትዮጵያ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ሁሉ የሰረጸ ነው በማለትም ራሴን አልለጥጥም፤ እኔ ባለፍሁበት የቤተሰብና የጎረቤት ተጽእኖ በምድረ ኢትዮጵያ ያሉ ሰዎች ሁሉ አልፈዋል አልልም፤ ለእኔ ስሜን መስፉን ብለው ያወጡልኝ አንዲት እማማ አልጋነሽ ስላቸው የነበረ የእናቴ ባልንጀራ የትግራይ ሴት ናቸው፤ እሳቸው መስፉን የሚሉት መስፍን ሲባልባቸው አልተቆጡም፤ ነገር ግን በቄስ ትምህርት ቤትም ሆነ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በአሳለፉኋቸው ዓመታት ከመላ ኢትዮጵያ ከመጡ ጓደኞች ጋር አድጌአለሁ፤ የብዙ ኢትዮጵያውያን ጎሣዎች ዘፈኖች ደስ እያለኝ ዘፍኛለሁ፤ ጭፈራቸውንም ደስ እያለኝ ጨፍሬአለሁ፤ እነዚህ ዘፈኖችና ጭፈራዎች ሁሉ በኢትዮጵያዊነታቸው የኔ ናቸው ብዬ አምናለሁ፤ ከትምህርት ቤት ስንወጣም እንጀራና ወጡ፣ ቆጮና ክትፎው፣ ገንፎና ጨጨብሳው፣ የኔ ናቸው እያልሁ ነበር፤ ጋቢውና ብሉኮው፣ ዳቦው፣ ቂጣውና አምባሻው፣ ወጡ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር የምጋራቸው ናቸው ብዬ አምናለሁ፤ ሊነጥቁኝ የሚፈልጉትን አልፈቅድላቸውም።

ኢትዮጵያውያን አንድ የማይካድ ዝንባሌ አለብን፤ መናገር እንወዳለን፤ የምንናገረውን ብናውቅም ባናውቅም ለመናገር

እንሸቀዳደማለን፤ በዚህ መጽሐፍም ጉዳይ ያየሁት ይህንን እምነት የሚያጸና ነው፤ አንዳንዶቹ ትችት አቅራቢዎች በእኔ ግምት ፊደላቸውን ጠንቅቀው ከማወቃቸው ሌላ ምንም የማያውቁ ሰዎች ናቸው ለማለት ይቻላል፤ አንዳንዶቹ ከርእሱ ውጭ ያላነበቡት በአደባባይ ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ ምንም ችግር አይታይባቸውም ነበር፤ ሳይፈቀድልን ሲቀር ጨዋነታችንን የምናስመሰክረው በዝምታ ነው፤ ከተፈቀደልን ግን ተናግረን አናባራም፤ ጊዜም አይበቃንም፤ አንድ ሰው በአደባባይ ንግግር አድርጎ ሲጨርስ አስተያየት ለመስጠት መድረኩ ሲከፈት ... ኢትዮጵያውያን አንድ ሰው ደፍሮ በሩን እስቲከፍትላቸው በጉጉት ይጠብቃሉ፤ ከዚያ በኋላ ይብላኝ ለስብሳቢው! እየተነሡ በልበ-ሙሉነት የባጡን፣ የቆጡን መቀባጠር ነው።

አንዱ የመክሸፍ ምክንያት በምንም ነገር ላይ ቢሆን የራሳችንን ጉድለቶች ለመስማት አለመፈለግ ነው፤ በቅርቡ በፋክት ላይ አይ አበሻ! በሚል አጠቃላይ ርእስ ስር *አበሻና ሆድ*፣ *አበሻና ልመና* በሚሉ ንዑሳን ርእስ ላይ ጽፌ ነበር፤ ሆዳሙና ለማኙ ሁሉ የስድብ ናዳ አወረደብኝ፤ የማያስተምር ከሆነ ብዬ ተውሁት፤ አንዱማ እኛ በሆድ እንዴት እንወቀሳለን በችጋር እያለቅን በማለት የምሩን ተናደደ! ጽሑፉን ጠንቅቆ አላነበበውም! መብላት የሚችሉት ከአስፈላጊው በላይ ባይበሉ ደሀውን ችጋር አይገርፈውም ነበር!

## ለምን አስደነገጠ? የእኔ የኢትዮጵያ ታሪክ ግንዛቤ

ኢትዮጵያውያን ብዙ የምንኮራበት ታሪክ አለን፤ ዞሮ ዞሮ የኩራታችንና የክብራችን ታሪክ አገራችንን ከውጭ ወራሪዎች ተከላክለን ከማቆየታችን ጋር የተያያዘ ነው፤ በትምህርትና በምርምር፣ በሥነ ጽሑፍና በሥነ ጥበብ፣በእውቀትና በፍልስፍና፣ ኑሮን ለማሻሻል በሚያስፈልጉ ዘዴዎች፤ በመመላለሻና በመገናኛ ዘዴዎች፤ በምህንድስናና በእጅ ሥራ ... ወዘተ. ምንም ዓይነት እድገትና መሻሻል አለማሳየታችንን ታሪካችን አያወሳም፤ አለማደጋችንንና አለመሻሻላችን ብቻ ሳይሆን ይህንኑ ጉድለታችንን ታሪካችን አለመዘገቡ የሚያሳፍረን ታሪካችን ነው፤ የራሳችን ፊደል ያለን ሕዝብ መሆናችን የሚያስኮራ በመሆን ፈንታ የሚያሳፍር





ይሆናል፤ ይህ መክሸፍ አይደለም የሚል ከመጣ በመክሸፍ ራሱን ያጽናና! ያለንበት አሳፋሪ ኋላ-ቀርነት የዚህ መክሸፍ ውጤት አይደለም የሚል ካለ ሌላ ምክንያት ማቅረብ ይጠበቅበታል።

የምንኮራበት ታሪካችን ተደጋግሞ ስለተነገረንና በሽለላና በፉከራ ተደግፎ ባህላችን ስለሆነ ጎልቶ ይሰማናል፤ያንን የኩራታችንና የክብራችን ምንጭ የሆነውን ታሪካችንን ለመጠበቅ ተከታታይ ትውልዶችን ብዙና ከባድ መስዋእት ከፍለዋል፤ በዚህም ምክንያት እስከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻ ዘመን ድረስ ተከታታይ ትውልዶች ለአገር ነጻነት ተጋድሎ ለመሰለፍ ግንባራቸውን አያጥፉም ነበር፤ አገራቸው ደኸዮች፣ ደከመች፣ አልመችም አለች ብለው የፈረንጅና የአረብ አሽከር ለመሆን አይሰደዱም ነበር፤ ቢሰደዱም በየሄዱበት ታላላቅ ሰዎች እየሆኑ ገናናና የተከበሩ እየሆኑ ይኖሩ ነበሩ፤ ይህ ሁሉ የክብራችንና የኩራታችን ቅርስ፣ የታሪካችን ሞገስ ነበር፤ዛሬ ይህ ቅርስና ውርስ አልከሸፈም የሚል ከመጣ ‹‹ጉድ ነው የአንኮበር ቅጠል!›› ከማለት በቀር ሌላ ምን ይባላል?[11]

·ሌላስ በታሪካችን የሚያሳፍረን ነገር የለም ወይ? ሞልቷል እንጂ! መቼ እንደተጀመረ የማይታወቀው የአንድ ትውልድ ስሕተት ወደሌላ ትውልድ እየተላለፈ ለብዙ ትውልዶች የስሕተት ምንጭ በመሆን ታሪካችንንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕዝብነት የበከለው መክሸፍ ዛሬም እንደቆላ ቁስል እየነዘነዘን እንዴት ይረሳል? እንደሚመስለኝ የመክሸፋችን ምንጩ ሦስት ነው፤--

አንደኛ፣ተቆጣጣሪና ተቆጪ የሌለው አገዛዝ ነው፤ የኢትዮጵያ አገዛዝ በመሠረቱ ሳይለወጥ ራሱን አስመስሎ ወራሹን እየወለደና እግዚአብሔርን የሙጢኝ እያለ ለብዙ ሺህ ዓመታት ቆይቶአል፤ የተመቸው ግፈኛ ሁሉ ለውጥን አይፈልግም፤ ምን ጎደለበትና ለውጥን ይፈልጋል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገዛዙ ተመቸ፤

[11] በሁለት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያን በሜዲቴራንያንና በቀይ ባሕሮች እየሰመጡ የሞቱ ስንት ናቸው? በታንዛንያ፣ በዛምቢያና በዚምባብዌ ስንት ኢትጵያውያን በእስር ቤት ተሰቃዩ? በሊባኖስ፣ በሳኡዲ፣ በኩዌይት በኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ ማቆሚያ አለው ወይ? ይህ ሁሉ ውርደት አያሰማንም ወይ?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገዛዙ ተመቸው ስንል ሕዝቡ የአገዛዙን ግፈኛነት በተግባር እየደገፈ ነው ማለት ነው።

በአለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ ደግሞ አዲስ የመክሸፍ መግለጫ ተከስቷል፤ ይህም ስደት ነው፤ በአገር ውስጥ ሆኖ ግፍን በሰላም መቀበልና ግፍን በስደት መሸሽ የመክሸፍ ሁለት ገጽታዎች ናቸው፤ ይህ ሁነት በአገዛዙ በኩል ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም በኩል ጥልቅ የሆነ ተደጋጋፊ መክሸፍን የሚያመለክት ነው፤ ማንም ኢትዮጵያዊ እናትና አባቱን ከሌሎች ዘመዶቹ ጋር ለግፍ አገዛዝ አስረክቦ እንደነጻ ሰው እየፎከረ እንቅልፍ ወስዶት የሚያድር አይመስለኝም፤ ኢትዮጵያ ነፍስ ነች!

ከስድሳ ስድስት አብዮት በኋላ ለስደት ሌላ ሰበብ ተገኝቶለታል፤ ይህም የብሔር ጭቆና የሚባለው ነው፤ የጉዳዩን ፍሬ-ቢስነት የሚያሳየው ዋናው ሐዋርያ ተብሎ የሚጠቀሰው ገና በትምህርትም ሆነ በልምድ ያልተፈተነ ዋለልኝ የሚባል ወጣት ነው፤ ሌላው ቀርቶ በማርክሳዊ-ሌኒናዊ ፍልስፍናና በጎሠኛነት መሀከል ያለውን ቅራኔ አልተገነዘበውም ነበር፤ መምህሩን ስታሊንን አጣጥሞ ቢያነበው ኖሮ የስታሊንን ጸጸት ስሕተትን አይዘራም ነበር፤ ለማናቸውም ጎሠኛነት ለስደት ተጨማሪ ሰበብ ሆነ፤ የሚያስደንቀው ግን የብሔር ጨቋኞች የተባሉትም ተጨቋኝ ነን የሚሉትም በስደት አብረው መሆናቸው ነው፤ ይህ ሁነት የሚያመለክተው ሁለቱም ጠባቸው ከኢትዮጵያ ጋር እንጂ እርስበርሳቸው አለመሆኑን ነው፤ አጥቂ የተባለውም ከተጠቂው ጋር ከተሰደደ ጥቃቱንም ይዘውት ሄደዋል እንዳንል እነዚያው አጥቂና ተጠቂዎች በኢትዮጵያ ውስጥም ያንኑ ጠባቸውን ይዘው እየተተራመሱ ናቸው፤ ከዚህ የበለጠ መክሸፍ ምን አለ?

ሁለተኛ፣የመክሸፍ ምንጭ የታሪክ ዘጋቢዎችና በአጠቃላይ ምሁራን የሚባሉት ናቸው፤ እስከዛሬም ድረስ ለሥልጣን በማጎብደድና ለጥቅም በመገዛት ሁነትን ሁሉ በአገዛዙ መነጽር ብቻ እያዩ ያንኑ ስሕተት ለተከታታይ ትውልዶች እያስተላለፉ ስሕተቶቹ እንዳይታረሙ ያደርጋሉ።





አገዛዙንና የታሪክ ዘጋቢዎችን እንደዋና የመክሸፍ ምንጮች ማመልከት ስሩን መገላለጥ አይደለም፤ይህንን ሰፊ ሥራ እኔ አሁን እዚህ አልጀምረውም፤ ነገር ግን በተለይ ሁለት ስሮችን በጥልቀት መመርመር እንደሚያስፈልግ (የታሪክ ተመራማሪ ነን ለሚሉ!) አመልክቼ ለማለፍ እፈልጋለሁ፤ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶችና የኢትዮጵያ ባህሎች ለመክሸፍ ያበረከቱትን በስፋትና በጥልቀት መመርመር ግዴታ ይመስለኛል፤ በተለይ የክርስትና ሃይማኖት በአውሮፓና በአሜሪካ ያስከተለው የነጻነትና የእኩልነት መንፈስ ኢትዮጵያን አልነካም ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤ ሃይማኖት ግለሰቡን ከፈጣሪው ጋር የሚያያይዝ ሲሆን፣ ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ስም የአገዛዙ ረዳትና ደጋፊ መሆናቸው ሃይማኖቶቹን የፖሊቲካ ቀለም መቀባቱ አልቀረም።

እንደሌሎች አገሮች ሁሉ ሃይማኖቶች በየቤተ ክርስቲያኖቹና በየቤተ መስጊዶቹ የትምህርት ገበታን ዘርግተው ሲያስተምሩ ኖረዋል፤ በትምህርት ረገድ ኃላፊነቱን በፈቃዳቸው ተቀብለው እንደነበረ ግልጽ ነው፤ ስለዚህም በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ማተኮራቸውና የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል የሚረዳ እውቀትን ባለማስገኘታቸው፤ ትምህርታቸውም አእምሮን ከማስፋት ይልቅ የሚያጠብ በመሆኑ ሊወቀሱና የመክሸፍ ምንጭ ሆነዋል ለማለት ይቻላል፤ ከዚያም በላይ አገዛዙን ለመቆጣጠርና ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲያድርበት ለማድረግ የሚያስችላቸውን መንፈሳዊ ሥልጣን ተጠቅመውበታል ለማለት አይቻልም፤ ይህ ጉዳይ ዛሬ በ2007 ዓ.ም. ተባብሶ ቤተ ክርስቲያንም ቤተ መስጊድም የአገዛዙ ሎሌዎች በመሆናቸው ትንቅንቁ እየጠነከረ ነው።

ከሃይማኖቶቹ ጋር ተባባሪ የመክሸፍ ምንጭ ባህል ነው፤ ባህል የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠርንፎ (በወያኔ ቋንቋ ለመናገር) ይዞታል፤ ዱሮም፣ ዛሬም! የእርሻ መሬቱን ሲነጥቁት እሺ ብሎ ወደልመና የሚሰማራ፣ ገፍትረው ከቤቱ ሲያስወጡት መንገድ ላይ እየተኛ የሚለምን ሕዝብ ነው፤ ሙሉ ታጥቆ፣ ጠመንጃና ቦምብ ይዞ ‹ራበኝ› እያለ የሚለምን የዋህ፣ ሁሉንም ወደእግዚአብሔር እያስተላለፈ ቁጣውን ዋጥ አድርጎ የእግዚአብሔርን ተአምር

የሚጠብቅ ነው፤ ልጆቹም የፈረንጅና የአረብ አገልጋዮች ሆነው በመሰደዳቸው በአጠገቡ ረዳት የለውም፤ የወላጆቹን መብት የማያስከብር ልጅ መውለድ መክሸፍ አይደለም የሚል ማን ነው? ሆኖም ምን ጊዜም ቢሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የእግዚአብሔር ተአምር ርቆት አያውቅም።

ሦስተኛ፣ ምናልባት እዚህ ላይ አንድ ሌላ የመክሸፍ ምንጭ ልናመለክት እንችል ይሆናል፤ በኢትዮጵያ አካባቢ አንድም ከኢትዮጵያ የተሻለ የፖሊቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ሥርዓት ያለው አገር አልነበረምና ልምድ ለመቅሰምም ሆነ በውድድር ወደተሻለ ደረጃ ለመራመድ አልተቻለም፤ ስለዚህ መክሸፍ የኢትዮጵያ ችግር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የአካባቢው ችግር ነበር ለማለት ይቻላል።

በኢትዮጵያ ከትውልድ ወደትውልድ የተላለፈውን ስናይ አገዛዙና ታሪክ ዘጋቢዎቹ ከእውነት ጋር ትውውቅም ጉርብትናም የላቸውም፤ ሌላው ቀርቶ አንድ አገዛዝ ተሸሮ ሌላ በሚተካበት ጊዜ ትንሽ ቀዳዳን ፈጥሮ ቅሬታዎችን ለማሰማት እምብዛም ሙከራ አይደረግም፤ አንድ አገዛዝ ተሸሮ ወይም ተገልብጦ በሌላ ሲተካ ምንም አዲስ ነገር አይመጣም፤ አንዳንዴ ማውገዝ ወይም መንቀፍ ቢሰማ በወደቀው ላይ እንጂ ባለው ላይ አይሰማም፤ ስሕተቶችንና ጥፋቶችን እያነሡ የሚቀጥለው አገዛዝ የተሻለ የሚሆንበትን ዘዴ መወያየትና መከራከር አልተለመደም፤ ፍርሃት፣ ጥቅምና የሹመት ምኞት አደንዝዞን በትክክል መገመት ያቅተናል።[12]

መክሸፍ ክብር ሆኖ፣ መክሸፍ ሹመት ሆኖ፣ መክሸፍ ሀብት ሆኖ፣ መክሸፍ ልማድ ሆኖ፣ ባህል ሆኖ ጥበብ ሆነ፤ **በመክሸፍ ባህል ላይ እውነትን ለመጋረድ ቅኔ ተፈጠረ፤ ቅኔ ከመክሸፍ የተገኘ ትርፍ ነው፤** የኢትዮጵያ አእምሮ ሲሠለጥን የት እንደሚደርስ ቅኔ ትልቁና ዋናው ማስረጃ ነው፤ የቤተ ሃይማኖት

[12] *በመርማሪ ኮሚስዮን ሊቀ መንበር ሆኜ አንድ ከሰድሳዎቹ ጋር የተገደለ ደጃዝማች በወሎ ችጋር ጉዳይ ቀረበ፤ ለጥያቄዎች መልስ ሲመልስ በዚያን ጊዜም ጃንሆይ ከነሙሉ ሥልጣናቸው እንዳሉ አድርጎ፤ ለራሱ ከመከላከል ይልቅ የጃንሆይን ስም ለመጠበቅ ይጨነቅ ነበር፤ በጣም አሳዘነኝና በአነጋገሬ የጃንሆይ ሥልጣን ማብቃቱን ልገልጽለት ብሞክርም አልገባውም።*





ትምህርት መክሸፉ ያንን የአእምሮ ክህሎት ድንክ አድርጎ ማስቀረቱ ነው።

ሥልጣን ከከሸፈ፣ ትምህርት ከከሸፈ፣ ሥራ (እርሻ፣ ሽመና፣ የቤት ግንባታ፣ መገናኛና መመላለሻ፣) ከከሸፈ፣ ማኅበረሰቡ ከሸፈ ማለት ነው፤ ከሁሉም የባሰው መክሸፍ በየዘርፉ ለምዕተ-ዓመታት ሲካሄድ የነበረው መክሸፍ ሁሉ በአገዛዙና በምሁራኑ ተሸፍኖና ተጋርዶ ሳይታወቅ ከትውልድ ወደትውልድ መተላለፉ ነው።

ዛሬ በ2007 ዓ.ም. በፖሊቲካ ረገድም ሆነ በኑሮ (በኢኮኖሚ) አብዛኛው የሠለጠነው ዓለም ክፍል ወደኅብረት ወደመጠቃለል እያሰበና እየሠራ ባለበት ዘመን በኢትዮጵያ የሚታየው በአገዛዙ የተደገፈ መበታተን የብዙ ዘመናት የመክሸፍ ውጤት ነው፤ በዘመናችን ያለው አገዛዝ መክሸፍን እንደትልቅና ብርቅዬ ውርስ ተቀብሎት ወደመጨረሻው የጥፋት ደረጃ አድርሶታል፤ የዘለቄታውን የአገር ጥቅም በመሻርና ጊዜያዊ የግል ጥቅምን በማራመድ ሁለንተናዊ መክሸፍ በአገሩ ላይ ተስፋፍቷል፤ ይህንን በጣም ሰፊና አደገኛ ተግባር እዚህ ለመዘርዘር ያስቸግራል፤ አገዛዙ የመክሸፍ ሥርዓትን ማዘጋጀቱ ራሱ የመክሸፍ አዘቅት ነው፤ ይህ እርምጃ በአገዛዙ በኩል እንደሚከናወን የመክሸፍ ውርስ ብናየው የዘመኑ ትውልድም አገዛዙን ተከትሎ ጭልጥ ብሎ መጓዙ በማኅበረሰቡ በኩል የሚተላለፈውን የመክሸፍ ውርስ የሚያመለክት አድርገን ልናየው የምንችል ይመስለኛል፤ ለመክሸፋችን ኃላፊነቱ የአገዛዙ ብቻ ሳይሆን የተቀባዩና በሥራ ላይ የሚያውለው ሕዝብም ጭምር ነው፤ ኃላፊነቱን ከሕዝቡ ለማስወረድ መሞከር እንደተለመደው መክሸፍን ማራመድ ይሆናል።

ዋናውና ትልቁ የማኅበረሰቡ መክሸፍ የሚታየው በአዲሱ ትውልድ ላይ ነው፤ የአባቶቹንና የእናቶቹን ቁስል እያሸና እየፋቀ እንዲተክዝ፣ በኢትዮጵያዊነቱ መንፈሱን ከማጠንከር ይልቅ ጎሣውን እያሰበ እንዲያፍር እየሆነ ነው፤ ለዜግነት መብቱ እንዳይታገልና ድምጹን በኢትዮጵያዊነት እንዳያሰማ የሻረ ቁስል እያከኩ ለግል ዓላማ መግቢያ ቀዳዳ በሚፈልጉ ሰዎች ይማረካሉ፤

እውነቱን በሐሰት ጭቃ እያቦኩ የጎሣዎችን ታሪክ ያጎድፋሉ፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴን አገዛዝ አማራ የሚባል ጎሣ ይመራው ነበር፤ ማንም ለማጣራት አይፈልግም እንጂ እንዲያው ብዙም ሳልጨነቅ ትግሬውን አቶ አበበ ረታን፣ ኤርትራዊውን ቢትወደድ አስፍሐን፣ ኦሮሞውን አቶ ይልማ ዴሬሳንና ምክትላቸውን አቶ ቡልቻ ደመቅሳን፣ ወላይታውን አቶ ምናሴ ለማን መቁጠር እችላለሁ፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የእነዚህ ሰዎች ሁሉ ሥልጣን ቀላል አልነበረም።

ከአጼው ዘመን በኋላ በመጡት የወጠጤ አገዛዞች ልዩነት በጣም ጎላና አገዛዙ ጎሣንና ዜግነትን እያጋጨ ሆን ብሎ ዜግነትን እያዳከመ ጎሣን ያጠነክራል፤ ብዙ ወጣቶችም ቀስ እያሉ ወላጆቻቸው ተሸክመውት የነበረው የግፍ ቀንበር ይሰማቸው ጀመረ፤ ይህ የሚያስደንቅ አይደለም፤ ማንም ቢሆን ይሰማዋል፤ ነገር ግን ያንን የግፍ ቀንበር ከኢትዮጵያዊነት ዜግነት ጋር ማያያዙ ከባድ መክሸፍ ነው።

ሦስት ነገሮች አሉ፤እነዚህም የሁላችንም ኢትዮጵያ፣ በተለያዩ ዘመኖች በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ሥርዓት፣በተለያዩ ዘመናት ሥርዓቱን የሚያንቀሳቅሱት ሰዎች ናቸው፤ የመክሸፉ ስንኮፍ ያለው እነዚህን ሦስት የተለያዩ ነገሮች ለይቶ ለማየት አለመቻል ላይ ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ይህንን ሁሉ ከነገድለቱ ለመውረስ አይፈልጉም፤ መፍትሔው ነጻነት ነው ብለው በቅገርት ይነቃሉ፤ ቅገርት የምለው ለማዋረድ አይደለም፤ እውነቱን ለመግለጽ ነው፤ ማስረጃ የሚፈልግ ለአንድ ሰዓት ያህል ብቻ ኤርትራና ሶማልያ ያሉበትን ሁኔታ ያጥና፤ በሁለቱም አገሮች ያለው ሁኔታ በሽታው ያለው በሥርዓቱ ላይ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፤ ሕዝቡን ሁሉ በነጻነትና በእኩልነት የሚያቅፍ ሕጋዊ ሥርዓት ከሌለ መበታተኑ የማይቀር ይሆናል፤ መበታተኑም ቢሆን አይቆምም።

ግን ማን ነው ነጻ የሚወጣው? ከማንስ ነው ነጻ የሚወጣው? የወያኔ ፕሮግራም ኢትዮጵያን አማራ አድርጎ ሌላው ሁሉ እንደኤርትራ ከ«አማራ» ነጻ እንዲወጣ ነው፤ ተገነዘቡትም አልተገነዘቡትም የኢትዮጵያን ታሪክ ሁሉ አማራ ለሚሉት





አስረክበው ባዶ እጃቸውን ነጻ ሊወጡ ነው! ግን አስቸጋሪ ነው፤ ኢሳይያስ አፈወርቅ የሆነለት በመንግሥት ደረጃ የኢትዮጵያን የቀን አቆጣጠር በፈረንጆቹ መለወጥ ብቻ ነው፤ ዛሬም ኢትዮጵያዊነት በኤርትራ ውስጥ ጎልቶና ደምቆ ይታያል፤ራሱ ኢሳይያስ አፈወርቅም ቢሆን ኢትዮጵያዊነቱን በውስጡ ቀብሮ ይዞአል፤ ይህ እኔ ራሴ ያረጋገጥሁት ነው።

በወላጆች ላይ የደረሰውን ግፍ እያስታወሱ ዛሬ ያንን ምክንያት አድርጎ ነጻነትን የሚሻው ግለሰብ ነው? ቤተሰብ ነው? ኅብረተሰብ ነው? በእርግጠኛነት ለመናገር የሚቻለው በትኛውም ኅብረተሰብ ቢሆን በአባሎቹ ሁሉ ላይ ግፍ አልተፈጸመበትም፤ በእያንዳንዱ ኅብረተሰብ ውስጥ ግፍን ተቀባይ ብቻ ሳይሆን ግፍን ፈጻሚና አስፈጻሚም ነበሩ፤ በዝርዝርና በማስረጃ ከተጠና የአንዱ ቋንቋ ተናጋሪ በሙሉ ግፈኛ፣ የሌላው ቋንቋ ተናጋሪ በሙሉ ግፍ ተቀባይ የሆነበት ታሪክ ያለ አይመስለኝም፤ ስለዚህም ነጻነትን የሚሹት ግለሰቦችና ቤተሰቦች ይሆናሉ፤ ማኅበረሰቡ በፊትም የተከፈለ አሁንም የተከፈለ ይሆናል፤

መፍትሔ የተባለው ዘዴ ጥያቄዎችን ያስነሣል፤ የማን ነጻነት? በጭቆና ሥርዓት ስር ለሞቱት ነጻነትን ልናስገኝላቸው አንችልም፣ ለጭቆናው ሥርዓት የሞቱትን ነጻ ለማውጣት ባይቻልም በጭቆና ስር እንደነበሩ ልንዘግባቸው ይገባል፤ ዛሬ ዓለም ወደዚህ የመንፈስ ከፍታ እየደረሰ ነው፤ ያለፈውን ጭቆና በጸጸትና በንስሐ ማጠብ እየተለመደ ነው፤ ሌላ መሠረታዊ ጥያቄም ያስነሣል፤ ባለፉት ሥርዓቶች ወገኖቻችን ተጠቁ በማለት ሮሮ ማሰማታቸው ተገቢ ሆኖ ሳለ አንዳንዴ ወደጨዋታነት ያዘነብላል፤ ትናንትና የነበረውን ሁኔታ በእውነተኛ መልኩ ለመግለጽ ያስቸግር ይሆናል፤ ነገር ግን ዛሬ እየሆነ ያለውና የምናየው ለትናንትናው ሁኔታ ምስክር ሊሆነን የሚችል ይመስለኛል፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴም ሆነ በደርግ የአገዛዝ ዘመኖች በመንግሥት ከፍተኛ ሹማምንት፣ በዓየር ኃይል፣ በጦር ሠራዊትና በባሕር ኃይል ሹማምንት፣ በሌሎች የመናግሥት መሥሪያ ቤቶች ሁሉ የሚገኙት ኃላፊዎች የነበራቸው •የጎሣ ስብጥር ታስቦበት የተደረገ አልነበረም፤ መመዘኛው ጎሣ፣አልነበረም፤ ዛሬ ከወላይታ

ጠቅላይ ሚኒስትር መሾሙ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን የነበረውን ለማያውቁ ለብዙ ሰዎች አዲስ ነገር መስሎ ይታያቸው ይሆናል፤ ግን አዲስ አይደለም፤ በሁለቱም የቀድሞ አገዛዞች ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች ከወላይታ ነበሩ፤ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የጦር መኮንኖችም ሆኑ ሚኒስትሮች በጎሣ ድርሻ ባይደለደሉም የጎሣ አድልዎ ነበረ ለማለት ያስቸግራል፤ ሌላ ቀርቶ አማርኛ ማወቅም ወሳኝ ነበረ ለማለት አይቻልም፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ጎሣ መደበቁ ማንን እንደጠቀመና ማንን እንደጎዳ የወደፊት ታሪክ ተመራማሪዎች ይጨነቁበት፤ አሁን ግን እንደግልጽ የታሪክ መክሸፍ ማየት ይኖርብናል፤ የታሪክ ሊቃውንቱ ይቺን እውነት እንኳን ደፍረው አልነገሩንም፤ አነግ የተጸነሰው በዚህ የታሪክ ክሽፈት ላይ አይደለም?

የዛሬውን እናቆየውና ስለትናንቱና ስለትናንት ወዲያው አገዛዝ እናውሳ፤ አንደኛ የምንስማማበት ሁሉም ጨቋኞች ነበሩ፤ ሁለተኛ በአድልዎ ከጭቆና ነጻ የነበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍል አልነበረም፤ ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የጭቆና ሰለባ ነበር፤ ይህንን ማለት ጭቆና አገዛዙ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የመለመላቸው ለጭቆናው መሣሪያ ያደረጋቸው ሰዎች አልነበሩም ማለት አይደለም፤ እንዲያውም አገዛዙ ከላይም ይሁን ከታች ጋብቻን መሣሪያ እያደረገ እያዛመደና እያዋለደ ነበር፤ የቱ የኢትዮጵያ የታሪክ ሊቅ ይህንን ዋና ማኅበራዊ-ፖሊቲካዊ ታሪክ አጥንቶ ዘግቦታል? ስንት እቴጌዎች ከደቡብ ነበሩ? ስንት ነገሥታት፣ መሳፍንትና መኳንንት ከተለያዩ ጎሣዎች ተወልደዋል? ንግሥት እሌኔንና ራስ አርአያ ዮሐንስን ብቻ ማንሣቱ ይበቃል፤ ይህ ሁሉ የታሪካችን ጭለማ መክሸፍ አይባልም?

ይህ ሁሉ ከተባለ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ በአጠቃላይም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች በጎሣዎች መሀከል መናናቅ አልነበረም ለማለት አያስደፍርም፤ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የነበሩ የገጠ መደቦች ከነሱ ውጭ የነበረውን ሁሉ አይንቁም ነበር ለማለት አይቻልም፤ የንቀቱ መሠረት ምን እንደሆነ የማኅበረሰብ ሊቃውንቶቹ በድኅማ ከሚያስጠኗቸው ሌላ በጥልቀት አልሞከሩትም፤ ከጎሣ መሠረት ይበልጥ በሥራቸው የሚናቁ





ነበሩ! ይህ በሁሉም ጎሣዎች ውስጥ የነበረ ነው፤ በጎሣዎች መሀከል ሳይሆን የተለያየ ሙያ ባላቸው ሰዎች መሀከል ነበር፤ የጋብቻ ድንበር ወይም እገዳ የሚጣለው በነዚህ ቡዳ በተባሉ ባለጆች› ላይ ነበር፤ በግልጽ የሚታየው ለማደግና ለመሻሻል የነበረው እንቅፋትና የትምህርት መክሸፍ ነው።

ኢትዮጵያን፣ ማኅበረሰቡንና ታሪኩን ከአገዛዙ ጋር በትክክልና እውቀትን በሚያዳብር መልኩ ለማጥናት አስተሳሰባችን የተዛባ እየሆነ ነገሮችን በተገቢው መንገድ የማፍታታት ልምዱ አልነበረንም፤ ለምሳሌ ቀደም ሲል የተገለጹትን ልዩነቶች በተገቢው መንገድ አናያቸውም፤ አንድ ሰው ቋንቋው አማርኛ ሆኖ ሃይማኖቱ እስልምና ቢሆንና ሌላው ሰው ቋንቋው ኦሮምኛ ቢሆንና ሃይማኖቱ እስልምና ቢሆን እነዚህ ሁለት ሰዎች በሃይማኖት ማንነት አንድ ሲሆኑ በቋንቋ ማንነት ይለያያሉ፤ እንዲሁም አንድ ትግሬ በሃይማኖቱ ተዋኅዶ የሆነ ቋንቋው አማርኛ ከሆነ፣ ኦሮምኛ ከሆነ፣ ጉራግኛ … ሰው ጋር የሃይማኖት ማንነትን ይጋራል፤ የበለጠ ውስብስብ ካደርግነው አንድ ሰው ቋንቋው አማርኛ ሆኖ ሃይማኖቱ እስልምና፣ ክፍለ-ሀገሩ ወሎ፣ ሌላው ደግሞ ቋንቋው አማርኛ ሆኖ ሃይማኖቱ ተዋኅዶ፣ ክፍለ-ሀገሩ ሸዋ ሲሆን የማንነታቸው ክር ሦስት ይሆንና የሚያገናኛቸው ማንነት ይሳሳል፤ እንዲሁም ቋንቋው አሮምኛ የሆነ የሸዋ ሰው ሃይማኖቱ ተዋኅዶ ሲሆን የማንነት ክር ይሳሳል፤ ይበልጥ እናወሳስበው ምና ሸዋ? ምና ወሎ? … እያልን የማንነት ክሩን እያሳሳን ችግራችንን ማባዛት እንችላለን።

የቋንቋንም፣ የሃይማኖቱንም፣ የክፍለ-ሀገሩንም ማንነት አልፎ የሚሄድና የሚጠቀልላቸው ማንነት ዜግነት ነው፤ አንዱ ዋና የመክሸፍ መገለጫው ዜግነት የሌሎች ንዑሳን ማንነቶች መቋጠሪያ መሆኑን የመቀበል ደረጃ ላይ ገና አለመድረሳችን ነው፤ በጣም ረጅም ከሆነ አብሮ የመኖር ታሪክ በኋላ! ይህ የሕዝብ ጉድለት ሳይሆን የአገዛዙ ተንኮል የፈጠረው ችግር ነው።

የዜግነት ሶላው ስያሜው ኢትዮጵያዊነት ነው፤ ትግሬ ነኝ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፤ ኦሮሞ ነኝ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፤ … እየተባለ በጎሠኞች ኅብረት ላይ የተመሠረተው

ሥርዓት በሰከነና በጥልቅ ጥናት መሠረቱን ለማግኘት አልተሞከረም፤ ቀደም ሲል እንደጠቀስሁት በጎሣዎች መሀከል ወይም በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መሀከል የሚከሰት መናናቅ በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲታይ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፤ መናናቅ የሚታየው በተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች መሀከል ብቻ አይደለም፤ በእያንዳንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ኅብረተሰብ ውስጥ መናናቅ ኤለ፤ እንዲህ ዓይነቱን ስሜት የማራባት ፍላጎት የለኝም እንጂ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፤ ለምሳሌ በአማርኛ ተናጋሪዎች መሀከል የመንዜዎች ቂልነት፣ የጎጃሜዎች ቡዳነት ሰዎች ሲፈለግ ለቀልድ፣ ሲፈለግ ለማሳነስ ሲጠቀሙበት የነበረ ነው፤ የትም ተወለድ አንኮበር እደግ የሚባለውም ያው ነው፤ እንዲሁም ስለጉራግኛ ተናጋሪዎች ብዙ ይባላል፤ እንዲህ ዓይነቱ ነገር በሌሎች አገሮችም እኔ እንኳን በደንብ የማውቀው በህንድ ስለሲኮች መቀለጃነት፣ በአሜሪካም ስለቴክሳኖች የሚነገረው ቀልድ ሁሉ ‹አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ›› ዓይነት ነገር ሞልቷል፤ የመረረና አብሮ መብላትንና መጋባትን የሚያግድ ንቀት ቀደም ሲል የተነጋገርነው ነው፤ በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ስሞችን እየጠቀሱ ማስረዳት ይቻል ነበር፤ ግን አስፈላጊ አይመስለኝም፤ **ፍሬ ነገሩ መናናቅ በተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች መሀከል ብቻ ሳይሆን በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ውስጥም መኖሩን ማወቅ ነው።**

የማኅበረሰብና የታሪክ ሊቃውንቱ ያልዳሰሱት ሌላ ትልቅና ዋና ጥያቄ ሰዎች በማናቸውም ምክንያት በውስጣቸው ያለውን ማኅበራዊ ቅራኔ አገዛዙ በተለያዩ ሰዎች ላይ ከሚያደርሰው ግፍ ለይቶ ለማየትና ለማስረዳት አለመቻል የትምህርቱን መክሸፍ ብቻ ሳይሆን በምኑም በምኑም እያዳለጠን የምንወድቅ መሆናችንን የሚያሳይ ነው፤ በዘመናችን ትልቁ የማኅበረሰባዊና የፖሊቲካ ችግር የሆነው ማኅበረሰባዊ ግፍን ተንተርሶ ለመጣው ችግር መፍትሔ ማግኘት አለመቻላችን ነው፤ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሰፈነውን የማሰብ ክሽፈት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ ይህንን እውነት ለማስረዳት ወደመላ-ምት አንገባም፤ ኤርትራ ግዙፍ **ማስረጃ** ነች፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት አገዛዞች ሁሉ በኤርትራ **ላይ** በደል ፈጽመዋል ቢባል አንደኛ በደል የተባለውን ማጣራትና





መፈጸሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ ሁለተኛ ትክክለኛውን መፍትሔ ለይቶ ማወቅ ያሻል።

ችግሩ ሁሉ ከአገዛዝ ጋር የተያያዘ መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ በሰዎች ላይ መላከኩ ቀላልና ብዙ ማሰብን የማይጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴና የደርግ አገዛዝ የ‹‹አማራ›› ሆነው በመፈረጃቸው ውግዘቱ ሁሉ ያንን ቋንቋ በሚናገሩ ሰዎች ላይ ተወረወረ፤ አስተሳሰቡ ቀላል በመሆኑ ዛሬም የወያኔን አገዛዝ የትግሬ አገዛዝ የሚያደርጉት አሉ፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴንና የደርግን አገዛዝ ከአማርኛ ተናጋሪው ጋር የሚያያይዙት በነዚህ አገዛዞች አማርኛ ተናጋሪዎች ደልቷቸውና ተመችቷቸው፣ የቋንቋው ተናጋሪዎች ሁሉ በገዢው መደብ ውስጥ የተጠቀለሉ አድርገው ይመለከቷቸዋል፤ እንዲሁም ወያኔን ከትግሬ የማይለዩና ትግሬዎችን ሁሉ የገዢው መደብ አካል ያደርጓቸዋል፤ ሁለቱም አስተሳሰቦች ከእውነቱ በጣም የራቁ ናቸው፤ ከተዛባ አስተሳሰብ የሚመነጭ ስሕተት ነው።

የለውጥ እንቅስቃሴዎች

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከኢጣልያ ወረራ በኋላ በእሳቸው ላይ በተነሡ እንቅስቃሴዎችና ሴራዎች ሳይደናገጡ፣ ወይም እንደማስጠንቀቂያ ሳይወስዷቸው በማሸነፋቸው ብቻ እየተኩራሩ የአገዛዝ ዘመናቸውን ገፉ፤ ሌላው ቀርቶ ጃንሆይ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በፍርድ ቤት ያደረገውን ንግግር የሰሙት፣ ቢሰሙትም ከቁም-ነገር የቆጠሩት አይመስለኝም፤ በዘመናቸው፡

1. የነቢትወደድ ነጋሽ ሴራ በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ከሸፈ.
2. የነደጃዝማች ታከለ ሴራ ከሸፈ.
3. የነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የስዒረ መንግሥት ሙከራ በጄኔራል መርዕድና በጄኔራል ከበደ ገብሬ ከሸፈ.

የአጼ ኃይለ ሥላሴ አዳፍኔ ሥርዓት ጉልበተኛነቱን እያፈረጠመና የገነባውን ሁሉ እያፈረሰ በክብር ቀጠለ፤ በዓለም መንግሥታት ማኅበር የተወሰነ የኤርትራን የአብሮነት (ፌዴሬሽን) መንግሥት አስገኘ፤ በኤርትራ የተፈጠረውን ማኅደረ ሥልጣን ወይም የፖሊቲካ ቤት ለማፍረስና ብቸኛ የማኅደረ ሥልጣን ባለቤት ለመሆን በመጓጓት የአብሮነት መንግሥቱን አፍርሰው ወደውጎደት ለወጡት፤ አብሮነት ከውጎደት ጋር ከሸፈ፤ ይህ የመክሸፍ ታሪክ ወደ1967 ዓ.ም. ቀጥሎም ወደ1983 ዓ.ም. አልደረሰም የሚል ሰው አለ? ከዚህስ በኋላ የመክሸፉን ጉዞ የሚያቆመውን የተደራጀ ኃይል የሚያይ አለ?

በዝምድናም በአብሮ-አደግነታቸውም ቅርብ የሚሆኑትን ልዑል ራስ እምሩን አንዴ በሶቭየት ኅብረት፣ አንዴ በአሜሪካ አንዴ በህንድ አምባሳደር እያደረጉ በማራቅ በእኩያነት የሚያነጋግራቸውን ሰው አጡ፤ ከፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትም ጋር ባለመስማማት ለስደት ዳረጓቸው።

ልዑል ራስ እምሩ በህንድ አገር አምባሳደር በነበሩ ጊዜ አንድ ቀን ስናወራ በጎረምሳ መንፈስ ደፍሬ አጼ ኃይለ ሥላሴን ለምን ዝም ይሏቸዋል፣ ለምን አንድ ነገር አያደርጉም? ስላቸው ፊታቸው ልውጥ አለና ‹‹መስፍን! ከሳቸው ጋር ዘመድ መሆኔን አታውቅም እንዴ? ከዚያም በላይ እሳቸውና እኔ ያደግነው አብረን በራስ መኮንን ቤት ነው፤ ምን አድርግ ነው የምትለኝ?›› ሲሉኝ አፈርሁ፤ ምንም ነገር ልመልስ አልቻልሁም፤ በራስ እምሩ መልስ ላይ ብዙ ጊዜ አስቤበታለሁ፤ የአገር ጉዳይና የዝምድና ቁርኝት፣ ለአገር ታማኝ መሆንና ለዝምድና ታማኝ መሆን፣ ... ለእኔ በግል ግን ራስ እምሩ ሚዛናቸውን ለእኔ እንዳጋደሉት አሳይተውኛል፤ አንድ ጊዜ ወደቤታቸው አስጠርተውኝ ሄድሁና በቤተ መንግሥት ውስጥ ራት ላይ ሲዛቱብኝ ስለሰሙ እንድጠነቀቅ ነገሩኝ፤ በዚያው ሰሞን ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴም አስጠንቅቀውኛል፤ እሳቸው ደግሞ ከእኅታቸው ከልዕልት እጅጋየሁ ሰምተው ነው።

ራስ እምሩ ስለዝምድናቸው ሲያስቡ አጼ ኃይለ ሥላሴ ግን ስለሥልጣን ያስቡ ነበር፤ ሁለቱን ሰዎች የሚነዳቸው ስሜት





በጣም የተራራቀ ነበር፤ በአንጻሩ አጼ ኃይለ ሥላሴ ለኢጣልያ ባንዳዎች የነበራቸው ፍቅርና እምነት ከፍተኛ ነበረ፤ ለዚህም ማስረጃው በቤተ መንግሥት ለቅርብ አገልጋይነት የመረጡት ባንዶችን መሆኑ ነው፤ አልባሻቸው ብላታ አድማሱ ረታ፣ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ልዩ ጽሕፈት ቤት የሚመሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅና፣ ከሳቸው የማይለዩት ጠባቂያቸው ጀኔራል መኮንን ደነቀ፣ ሁሉም ባንዳዎች ነበሩ፤ እነዚህ በጣም ትርብና በየቀኑ የሚገናኙ ነበሩ፤ በተጨማሪም በሚኒስትርና በጦር አዛዥነት ደረጃ በየመሥሪያ ቤቱ ነበሩ፤ ከመሳፍንቱም ውስጥ ሆነ ከመኳንንቱ ውስጥ ብዙ ባንዳዎች ነበሩ።

## ማኅደረ ሥልጣን ወይም የፖሊቲካ ቤት

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አገዛዙን ዘመናዊ ለማድረግና ሥርዓት ባለው መንገድ ለውጥ ለማምጣት ማኅደረ ሥልጣኑን ወይም የሥልጣኑን ቤት ለማብዛትና ለማስፋት የሚቀጥሉት ሙከራዎች ተደርገው ነበር፤

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ተቋቋመ፤
የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ተቋቋመ፣
የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተቋቋመ፣
የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማኅበር፣ተቋቋመ፤

ሁሉም ከሸፉ!

በሌላም በኩል የሚከተሉት የማኅደረ ሥልጣን ጽንሶች ሞቱ፤

የጦር ኃይሎች ኅብረት (ደርግ) ተቋቋመ፣
የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ተቋቋመ፣
የመላው ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ ተቋቋመ፤

ሁሉም በውስጣቸው ባዘሉት አዳፍኔ ታግዘው ከሽፉ፤ ያዘሉት አዳፍኔ የምለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአስተዳደጉና በባህሉ ያደረበትን የሥልጣን ጥም ነው፤ ይህንን ያልተገነዘበ የኢትዮጵያ ፖሊቲከኛ ገና ራሱን ያላወቀ ነው፤ ወይም አውቆ ራሱንም ሕዝብንም ለማታለል የሚሞክር ነው።

## ደርግና ወያኔ

ደርግና ወያኔ የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ የባሕርይ ልጆች ናቸው፤ ዘመናዊነት ባለጌዎች አድርጓቿል፤ አጉል ማርክሳዊ-ሌኒናዊነት እግዚብሔር-አልባ አድርጎአቸዋል፤ ትዕቢት ወደይሉኝታ-ቢስነት ለውጦአቸዋል፤ በተረፈ አዳፍኔ በውስጣቸው ተጠናክሮ ጎጆውን ሠርቷል፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በካባ ተሸፋፈኖና በባህል ገመድ ተሳስሮ የነበረው አዳፍኔ ስድ ሲለቀቅ ወደጭራቅነት ተጠጋ፤ የሰው ሕይወት ዋጋ አጣ፤ የሕዝብ ንብረት የጥቂቶች ቁማር መጫወቻ ሆነ።

መሀይምነትና አላዋቂነት የሥልጣን ማድመቂያ ሆኖ በፈረንጅ አገር ኪዮስኮች በርካሽ በሚገዛ ማኅተም ብቻ ባለበት ባዶ ነጭ ወረቀት ያጌጣል፤ በነጭ ወረቀት ዶክተር፣ ፕሮፌሰር፣ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ የመንግሥት አማካሪ፣ የዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ተጠሪ፣ … ለመሆንና ምንም ሳያፍሩ ያልሆኑትን መስሎ በመታየት የሚኩራሩ አሉ፤ ሌላውም ውስጡን ለቁስ እያለ በንቀት እያየ ያልፋቸዋል።

በወና ጭንቅላታቸውና በድፍን ልባቸው የተናቁ ገዢዎች በፍርሃት በደነዘዙና በደመ-ነፍስ በሚነዱ ተገዢዎች በመክሸፍ ቀጭን ክር ላይ ሆነው እየተሳሳቡ ወደጉድጓዱ ይገባሉ። የኢትዮጵያ ትራፊክ ይመስክር! ይህንን በምጽፍበት ጊዜ የወያኔ መሪዎች የተማረው የመንግሥት ሠራተኛ ለውጥ ፈላጊና ጸረ-ኢሕአዴግ ነው አሉ የሚል ወሬ እየተናፈሰ ነበር!





# ምዕራፍ ፪
# መቅድም

## ከወላጆቻችን የተረከብነው

የምዕራባውያን ኃይሎች ሀብትና ጉልበት አላቸው፤ በጉልበት የማይችሉትን በገንዘብ እየገዙ፣ በገንዘብ አልገዛ ያላቸውን በጉልበታቸው እየቀጠቀጡ ተገዢ ያደርጋሉ፤ እነዚህ ምዕራባውያን ኃይሎች ኢትዮጵያን ኢላማ አድርገዋታል፤የልጆችዋን ኩራትና ክብር ኢላማ አድርገዋል፤ ኩሩ ልጆችዋን መሸጦ ለማድረግ በገንዘብም በጉልበትም የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ነው፤ ስለዚህም ኢትዮጵያ ተክዛለች፤

ውርደትንና ከሰው በታች መታየትን የሚጸየፉ፣ ደሀዎች ሆነው ክብራቸውን የሚያስከብሩ ኩሩዎች፣ ያልተማሩ ቢሆኑም፣ አንኳን ይቺን የዝንብ ጠንጋራ እናውቃለን የሚሉ አዋቂዎች፣ የመማሪያ ብልጫ ላለው ጉልበተኛ እጅ ያልሰጡ ጀግኖች፤ ቱርኮች፣ በአረቦችና በምዕራባውያን የቅኝ አገዛዝ ወጥመድ ውስጥ ያልገቡ ብልሆችና ጀግኖች፡--- እነዚህ ትውልዶች አልፈው ኢትዮጵያ ጫትና አንክርዳድ አበቀለች፤ ስለዚህም ተክዛለች

ዛሬም ሌላ ቢቀር የኢትዮጵያን መተከዝ በማስተዋል የሚያዝኑ፣ የሚቆረቆሩ፣ የሚበሳጩና የሚናደዱ ልጆች አሏት፤ እነዚህ ሽለላ፣ ቀረርቶና ፉከራ ዘፈን ከሆነ በኋላ የተወለዱ ልጆች ናቸው፤ሽለላ፣ ቀረርቶና ፉከራ የአገራቸውንና የወገናቸውን፣ ክብርና ኩራት በሕይወታቸው ለመጠበቅ ጀግኖች በአደባባይ ለማኅበረሰብ ቃል ኪዳን የሚገቡበት ሥርዓት ነበር፤ ዛሬ የክሽፈ ሥርዓት ነው፤

በዚህ ሥርዓት ስር ያደገው ትውልድ ቀረርቶ፣ ሽለላና ፉከራ ሲሰማ ደሙ በግምባሩ ላይ ይፈላበታል፤ ሆዱ የሸበርበታል፤ ለተግባር ጥሪ መሆኑን ያውቃል፤ ተግባርን ይናፍቃል፤ ለተግባር ዝግጁ መሆኑን በአደባባይ ያበሥራል፤ ለአገሩና ለወገኑ አለኝታ መሆኑን በቃል ኪዳኑ ያረጋግጣል፤ ወላጆቹና ዘመዶቹ፣ ወዳጆቹና ጓደኞቹ ያከብሩታል፤ ሚስቱ ወይም ወዳጁ ይኮሩበታል።

በዚህ ትውልድና ቀረርቶን፣ ሽለላንና ፉከራን ወደዘፈን በለወጠው ትውልድ መሀከል ትልቅ ገደል አለ፤ ከገደሉ ማዶ ሰውነት፣ ኢትዮጵያዊነት፣ ክብርንና ኩራትን ተጎናጽፈው በሙሉ ልብ አገሬ፣ ወገኔ ብለው ከሞቱት ጋር በአንድነት ቆመዋል፤ ከገደሉ ወዲህ ሰውነትና ኢትዮጵያዊነት ከስተውና ደብዝዘው፣ ሙሉ ልብ በጥርጣሬ ተንፍሶ፣ አገሬና ወገኔ የሚባለውንም ሀሳብና ስሜት በነገድና በጎሣ መንዝሮ የሚያይና ተበታትኖ ያለ ነው፤ ከገደሉ ማዶ ከፋም ለማም፣ ጠቀመም አልጠቀመም አገር አንድ ነው፤ ወገን አንድ ነው፤ ከገደሉ ወዲህ አገር ብዙ ነው፤ ወገንም ብዙ ነው፤ ከገደሉ ማዶ ባህል የኑሮ መሠረት ነው፤ የማንነት መገለጫ ነው፤ ከገደሉ ወዲህ ባህል ሸቀጥ ነው፤ ቅዱስና ክቡር የሆነ ነገር የለም፤ ከገንዘብ በቀር፤ ዶላር ከተገኘ ሁሉም ነገር፣ ሰውም ጭምር፣ የሚሸጥ ነው።

በነዚህ ታሪክ በቆፈረው ገደል ማዶ ለማዶ ሆነው፣ እንዳይለያዩ ተቆራኝተው፣ እንዳይፋቀሩ ባልነበሩበት የታሪክ ጠብ ተኮራርፈው፣ ወደፊት እንዳይራመዱ ገደሉን መሻገር ተስኖአቸው፣ ሳይቀራረቡ የሚተያዩ እንዲያውም ተፋጥጠው ገደሉን የሙጢኝ ያሉ ትውልዶች፣ በማያውቁት ታሪክ ተተብትበው ወደኋላ እንጂ ወደፊት መራመድ የማይችሉ ትውልዶች፣ በአእምሮ መንሸዋረር ባዕድን እንደዘመድ፣ ዘመድን እንደባዕድ እንዲመለከቱ የተገደዱ ትውልዶች፣ ራሳቸውን ሽባ አድርገው ችግሮቻቸውን ሁሉ ለመፍታት የፈረንጆችን እርዳታ የሚፈልጉ ትውልዶች፣ ይህንን ፍጹም መክሸፍ ማየትና የተተበተቡበትን የከሸፈ የታሪክ ገመድ መለወጥ ያቃታቸው ትውልዶች ኢትዮጵያን የአፍሪካ መሳለቂያ አድርገዋታል።





ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ ሁሉ፣ ኢትዮጵያውያን አይደለንም የሚሉ ሁሉ፣ ስደተኞች ነን የሚሉ ሁሉ፣ ለስደት ያኮበኮቡ ሁሉ በከሸፈ ታሪክ እየነገዱ፣ በከሸፈ ታሪክ እየተጣሉ፣ ለከሸፈ ኢትዮጵያዊነት እየተቆረቆሩ፣ የከሸፈ እንጀራ እየበሉ፣ በከሸፈ ቀረርቶ ራሳቸውን እያታለሉ፣ ስደት ለወሬ ይመቻል እንዲሉ አሽከርነታቸውን መኳንንት በመምሰል ይሸፍናሉ፤ አገራቸውን ጥለው ሄደው አገር እንዳለው ሰው በሰው አገር ሆነው ‹‹እኔም አገር አለኝ የሚታይ በሩቁ›› እያሉ ይዘፍናሉ፤ በሩቁ የሚታይና እናቶቻቸው ሲሞቱ የማይቀብሩበት፣ በአባቶቻቸው እግር-ብረት የማይገቡበት አገር፣ እንግዲህ ስደት ለወሬ ይመቻል የሚባለው ይሄ ነው።

## የቅርብ ታሪካችን

እስቲ የመጨረሻውን ዋናውን የኢትዮጵያን ታሪክ የውርደት ጥላሸት የቀባውን የቅርቡን ሁኔታችንን እናስታውስ፤ በ1928 ኢጣልያ እኛ በማናውቀው መንገድ በሰማይ በአውሮጵላን መጥታ የጋዝ መርዝ እየነሰነሰች የኢትዮጵያን ሠራዊት ከጥቅም ውጭ አደረገችው፤ ይህንንም ተከትሎ የኢጣልያ ወታደሮች ኢትዮጵያውያንን በእርግጫ እያሉ ለብዙ ሺህ ዓመታት ሲጋገር የቆየውን ኩራታቸውንና ክብራቸውን ከውስጣቸው አንጠፍጥፈው አስወጡባቸው፤ በዚህም የተነሣ በ1933 ዓ.ም. በኢትዮጵያውያን ነፍስ ውስጥ ሠርጾ የገባ የፈረንጅ አምላኪነት ተጀመረ፤ በአፍጢሙ የተደፋው ኩራትና ክብር እስከዛሬም ቀና የሚያደርገውን ትውልድ ሆነ መሪ አላገኘም፤ መጥፎ ዓይነት መክሸፍ ብቻ ሳይሆን መክሸፍን የሚያመርት ኃይል ከውስጣችን ይፈልቅ ጀመር።

እንዴት የኢትዮጵያውያን ኩራትና ክብር በአፍጢሙ እንደተደፋ በትክክልና በዝርዝር ለማወቅና ለማሳወቅ የሚፈልጉ የአእምሮ ሰዎች ለመሆን ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች ሁሉ በጻቸው ሁሉ በደጃቸው ነው፤ አዲስ ዘመንንና ‹‹ኢትዮፕያን ሄራልድ›› ጋዜጦችን ይዘው፣ ፕሮፓጋንዳውን ትተው ሁነቶችን ብቻ እየነቀሱ

አውጥተው፣ ሌሎች ምንጮችን ማመሳከሪያ እያደረጉ በተለያዩ መስኮች -- በትምህርት፣ በልማት ተቋሞች፣ በጦር ኃይሎች፣ በውጭ ጉዳይ፣ በአፍሪካ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ የነበራትን ደረጃ -- በትክክል ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አልጠራጠርም፤ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን ፍላጎት ስላልነበራቸው ጥቂት አርመኖችና ግሪኮች በኢትዮጵያ ድርሻ ይጠቀሙ ነበር፤ የትም አገር ለመሄድ ለኢትዮጵያውያን በሩ ክፍት ነበር፤ በአንዳንድ አገሮች ኢትዮጵያውያን ቪዛም አያስፈልጋቸውም ነበር።

የኢትዮጵያ ስም ገናናነትና የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ለአፍሪካ ሕዝቦች ነጻነት በብዙ በኩል ያበረከተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ፣ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የብቻቸው ቁርጠኛነት የአፍሪካ አንድነትን ለመመሥረት ያስቻለ መሆኑን በራስ መተማመን ላልተፈጠረባቸው፣ ኩራትና ክብር ከውስጣቸው ተራግፎ ለቀለላቸው የወያኔ መሪዎች የበለጠ የሚያቀላቸው መስሎ ስለታያቸው ለሌላና ለማይገባው ሰው በአዲስ አበባ ውስጥ ሐውልት እንዲሠራ አደረጉ፤ ደርግ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ባለሥልጣኖች ሁሉ ስለጨረሳቸው ትክክለኛው መረጃ በይፋና በሙሉ ባይወጣም፣ ከአልጄርያ እስከደቡብ አፍሪካ፣ በኬንያና በዚምባብዌ ለአፍሪካውያን የነጻነት ትግል ኢትዮጵያ ያበረከተችው ገና በሙሉ ለታሪክ ማኅደር የደረሰ አይመስለኝም፤ የመክሸፍ አባዜ ስለተጠናወተን ቀደም ያለው የሠራውን በኋላ የሚመጣው ያፈርሰዋል ወይም ይደብቀዋል፤ ታሪክን የአገርና የሕዝብ አድርጎ በመመልከት ፋንታ የግል በማድረግ ታሪክ ያለባሕርዩ እንዲያጥርና በሰው ዕድሜ እንዲለካ ይደረጋል፤ ታሪክ የሚከሽፍበት አንዱ መንገድ ይህ ነው።

እዚህ ላይ ሌላ ዋናና በጣም ትልቅ ገና ወጌሻ ያልተገኘለት የታሪክ ስብራት ያጋጥመናል፤ እስከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ ብቸኛና ዝነኛ አገር ነበረች፤ በደርግ ዘመን በቀይና በነጭ ሽብር አረመኔያዊ ጭፍጨፋ የኢትዮጵያ ታሪካዊ የመንፈሳዊ የቅርስ ክምችት ተናደ፤ ይህ ከመክሸፍ የባሰ መራቆት ነው፤ በእኔ ግምት በደርግና በወያኔ የአገዛዝ ዘመኖች የተፈጸመው መክሸፍ በፋሺስት





ኢጣልያ አሸናፊነት ከተፈጸመው መክሸፍ ጋር ሲወዳደር የባሰ ነው፤ እንዴት? መጀመሪያ ተከታታይነቱን ልብ እንበል፤ አንደኛ ፋሺስት ኢጣልያ ለብዙ ሺህ ዓመታት በውጭ ኃይል ሳይበገር የኖረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ፋሺስት ኢጣልያ ድል በማድረግ የዘመኑን አዲስ የእድገት ክፍታ አሳየች፤ በአንጻሩም ኢትዮጵያ ያለችበትን በጣም ዝቅተኛና ቆሞ-ቀር ደረጃ በተግባር አስመሰከረች፤ ይህ አዲስ እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የነበረውን አልበገር-ባይነት ከነኩራቱና ከነክብሩ ገፈፈው፤ የመንፈስ ኃይሉ ደቀቀ፤ አንገቱን ደፋ።

ሁለተኛ የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ በፋሺስት ኢጣልያ መሸነፉን እንደተቀበለ ቀጠለ፤ የዘመኑ ወጣቶች በውሸት ‹‹ድል አድራጊው ንጉሣችን›› እያልን እንድንዘምርና ሸሽተው ከሄዱበት ከስደት የተመለሱትን ንጉሠ ነገሥት ማወደስ ጀመርን፤ ቆም ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን ተሸነፈ? ዓለም በሰማይ ላይ መሄድ እስኪጀምር ድረስ እኛ የት ነበርን? ኢትዮጵያ እንደአገር መንና ገዳም .ገብታ ነበር? የኢጣልያን ኃያልነትና የእኛን ደካማነት በማያጠራጥር መንገድ ከተረዳንና ልካችንን ካየን በኋላ ወደነበርንበት መመለሳችን ምንን ያሳያል?

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኩራትና ክብር ፈጽሞ ደብዛው እንዳይጠፋ በዱር በገደሉ እየተሧሧሩ ኢትዮጵያዊ አልበገር-ባይነትን ለፋሺስት ኢጣልያና ለዓለም ያሳዩትን አርበኞችን ከስደተኞችና ከባንዶች በታች በማድረግ ፋሺስት ኢጣልያ ያደቀቀችውን የኢትዮጵያውያንን የመንፈስ ኃይል የስደተኛው የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ይበልጥ አደቀቀው፤ ይህ የእኔና ተከታታይ ትውልዶች ያለፍንበት የከሸፈ ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፋሺስት ኢጣልያ ድል አድራጊነት ቀንበር ገና ያልተላቀቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ስደተኞችና ባንዶች የኢትዮጵያን ሕዝብ የገዙበት ዘመን ነው።

ሦስተኛ፣ ተከታትለው ሥልጣን የያዙት የደርግና የወያኔ አገዛዞች ናቸው፤ ሁለቱንም በእውቀትና በትምህርት ስንመዝናቸው ገለባ ናቸው፤ በዚህም አያበቃም፤ ዋናውና ክፉው ነገር ገለባነትን ባህልና ሥርዓት አድርገው በወጣቱ ላይ መጫናቸው ነው፤

ቀድሞውንም ደርግና ወያኔ መሠረታቸው ወጣቱ ነበር፤ የተማሩትና ለሥልጣን የጓጉት ወጣቶች ገና ያልተማሩትን ሠራዊታቸው አድርገው መንበሩ ላይ ለመውጣት ትግል ሲጀምሩ፣ መጀመሪያ በወታደሩ ቀጥሎም በወያኔ ተቀደሙ፤ የተሸነፉት እንደአጼ ኃይለ ሥላሴ ስደትን የሙጢኝ ብለዋል።

የዚህ የአደገኛ መክሸፍ ውጤት ኢትዮጵያን ወደኋላ እየገፋና እያደበዘዘ ኢትዮጵያዊነትን በመደፍጠጥና ሌላ ሌላውን ወደላይ በማውጣትና በማድመቅ የመክሸፉን ጉዞ እያፋጠነና እያጠናከረ ነው፤ ይህንን ማንም ለማመን እንደማይፈልግ ይገባኛል፤ ማመን የሚያስቸግርበትም ምክንያት ራስን ወደመውቀስና ወደንስሐ፣ ከግለሰብ ወደአገር ከጊዜያዊ ወደዘለቄታዊ፣ ከአፍአዊ ወደመሠረታዊ ለውጥ በቁርጠኛነት መሸጋገር ግዴታ ስለሚሆን ነው፤ የዘመናዊው መክሸፍ ምንጭ የሆነው አብዛኛው ከአርባ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለውና የተማረ የሚባለው ትውልድ ስለንስሐ አያስብም፤በጥፋቱ ደንድኗል፤ እንዲያውም ለአገሩና ለወገኑ ከፍተኛ መስዋእት የከፈለ፣ ብዙ ሰማዕታትን ያፈራና ሳይሳካለት ቀርቶ ከፖሊቲካው መድረክ የተገፋ በመሆኑ እያላዘነ ታሪክን በተቃራኒው እያየ የሚኖር ነው፤ ከአርባ ዓመታት በላይ የራሱን ውዳሴ እየደገመ የቆየ በመሆኑ ለመለወጥ የሚቸገር ትውልድ ነው፤ ውሸት እውነትን አይወልድም፤ መጀመሪያ ሁኔታውን ለመረዳት የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን ሁሉ ለመጠየቅ የአእምሮና የመንፈስ ዝግጁነት ያስፈልጋል፤ ከሁሉም በላይ እውነትን ከሚያስከትለው ድፍረት ጋር መቀበል ያሻል፤ ይህ ቀላል አይደለም፤ እውነትን ለመቀበል የሚያስቸግረው አንዱ ከባዱና ዋናው ስጋት ከኃላፊነት ጋር የተያያዘ ነው፤ በመክሸፉ ውስጥ የነበሩ ሁሉ ኃላፊነትን ለመቀበልና ለምንጊዜም የመክሸፉን መንገድ ለመዝጋት መበረታታት ያስፈልጋቸዋል።







መክሸፍ ጠንካራ የአስተሳሰብ ባህል መሆኑን በአንድ አፍታ ለመገንዘብ በአዲስ አበባ በአንድ ሦስትና አራት መንገዶች በሚገናኙበት አካባቢ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ለአሥር ደቂቃ ያህል የመኪና ነጂዎቹን አነዳድ በማስተዋል መከሻሸፍ ምን ያህል ጠልቆ የገባ ባሕርይ እንደሆነ ይታያል፤መኪናዎቹን እያቆላለፉ ማንም እንዳይንቀሳቀስ ወይም ሁሉም ጭንቀት ውስጥ እንዲወድቅ መደራረግ ነጂዎች ሁሉ የተማሩት ሕግ ይመስላል፤ በአንጻሩ ለምሳሌ አንዳንድ በጣም ጠቃሚ የሆኑ የእርሻ አሠራሮች በጭራሽ አይሰራጩም፤ በጂሩ የሚታየው የጥቁር አፈር እርሻ ከዚያው ከአካባቢው አያልፍም፤ በኮንሶና በየጁ የሚታዩ የመስኖ ሥራና የእርከን እርሻ ጥበብ ከዚያው ከአካባቢው አይወጡም፤ የአዲስ አበባውን ትራፊክ ሁኔታና እነዚህን የጠቀስኋቸውን የእርሻ ዘዴዎች አብራችሁ አስቡአቸው፤ ለምንድን ነው ጥሩውና ጠቃሚው ዘዴ በሰፊውና በፍጥነት የማይሰራጨው? በአንጻሩ ለምንድን ነው ጠቃሚ ያልሆነው አጉል እልህ በቶሎና በሰፊው የሚሰራጨው? እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች በጥሞና ቢያስብባቸውና ቢፈታቸው መክሸፍ ከውስጣችን ይወጣል ብዬ አምናለሁ።

መክሸፍ የምለው አንድ የተጀመረ ነገር ሳይጠናቀቅ ወይም ሳይሳካ እንቅፋት ገጥሞት መቀጠል ሳይችል፣ ዓላማው ሲደናቀፍና በፊት ከነበረበት ምንም ያህል ወደፊት ሳይራመድ መቅረቱን ነው፤ የእድገት፣ የመሻሻል፣ የመለወጥ ጉዞ መቋረጥን የሚያመለክት ነው፤በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክ አብዛኛውን ጊዜ ከታችኛው ደረጃ ወደላይኛው ደረጃ የሚያደርስ፣ ከተጎሳቆለ ኑሮ ወደተሻለ ኑሮ የሚያመጣውን ጉዞ የሚያመለክት የእድገት ጎዳና ሆኖ ይታያል፤ አንዳንድ ጊዜ ግን አንዳንድ ሥልጣኔዎች ቶሎ ያብቡና ሳያፈሩ ቶሎ ይደርቃሉ፤ ደርቀው አይቀሩም፤ ተፈጥሮ ቆሞ መቅረትን አይደግፍም፤ ለውጥ ግዴታ ነው፤ ወደተሻለ ደረጃ ካልተለወጡ ወደባሰ ደረጃ መውረዱ የማይቀር ነው፣ ወይም በሌላ አነጋገር

ካላደጉና ካልተሻሻሉ ሶሻገትና መበስበስ፣ በስብሶ መፈራረስ ግዴታ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ መክሸፍ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ግዙፍ ቦታ የያዘ ይመስለኛል፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ የማውቀው አንድም ጥናት የለም፤[13] አንድም ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሁር ይህንን ጉዳይ የነካ አላውቅም፤ ይህ ራሱ ኢትዮጵያውያኑ የታሪክ ሊቃውንት ዓላማቸው ከኢትዮጵያ ውጭ መሆኑን፤ወይም ታሪክን የሚያዩት እንደተረት መሆኑን ያመለክታል፤ መነሻ የሌለው፣ አቅጣጫ የሌለውና ዓላማ የሌለው አድርገው በጊዜ በታጠረ ብቅ-ጥልቅ ውስጥ የሚነገር ተረት አድርገውታል።

ብዙም ወደኋላ ሳልሄድ ከእኔው ዕድሜ ልጀምር፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ የነገሡት በ1922 ነው፤ ከኢጣልያ ጋር ሲናቆሩ ሦስት ዓመታት ያህል ቆይተው ጦርነቱ ተጀመረ፤ ማይጨው ዘመቱና ወዲያው ተመለሱ፤ ወዲያው ተሰደዱ፤ አምስት ዓመታት በእንግልጣር ቆዩ፤ በ1933 ዓ.ም. ተመለሱ፤ ከኢጣልያ ወረራ በፊት የነበረውን እንጣለውና ከስደት ከተመለሱበት ብንጀምር የኢጣልያ ጦርነትና ወረራ ያስከተለው

1. በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሰው ግፍና ጭፍጨፋ፣ ውርደት፣
2. በአርበኞች ላይ የደረሰው መከራና ስቃይ
3. በአጼ ኃይለ ሥላሴ በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ የደረሰው ውርደትና እንግልት

የኢጣልያ ጦርነትና ወረራ ለአጼ ኃይለ ሥላሴና ለተከታዮቻቸው፣ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ምን አስተማረ? ይህ ያንን በኢጣልያ ወረራ ምክንያት የተሰቃየውን፣ በአርበኝነት የታገለውን፣ በስደት የቆየውን ትውልድ በግድ መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ነው፤ ይህንን ጥያቄ በአርምሞ መዝለል በዙ ዓይነት ኃላፊነቶችን ችላ ማለትና እውነትን ለመረዳት አለመፈለግ ነው፤

[13] የጥንቱ ሮም አወዳደቅ ብዙ ጥናቶች ተደርገውበታል፤ በሌሎችም የአውሮፓ አገሮች ተመሳሳይ ጥናት አለ፤ የውድቀቱን ወይም የመክሸፉን ምክንያት ካላወቁ እየከሸፉ መቀጠል የማይቀር ይሆናል።





ከዚያም በላይ ከ1933 ዓ.ም. በኋላ የሆነውን ሁሉ በሚገባ ለመረዳት አንችልም።

ጥያቄው ሳይጠየቅ አንድ ትውልድ አለፈ፤ እነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ፣ ወርቅነህ ገበየሁ፣ ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ... ጥያቄውን በጠመንጃ አነሡት፤ ለጠመንጃ መልሱ ጠመንጃ ነውና የጠመንጃ ጥያቄው በጠመንጃ መልስ ከሸፈ፤ ብዙ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ተሰቀሉ፤ ተሰቃዩ፤ ታሰሩ፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂዎች የነበሩት የክብር ዘበኛ ወታደሮች ዓምጸው ተፈርተው የነበሩት የጦር ሠራዊትና የዓየር ኃይል ክብር ዘበኛን ደብድበው የአጼ ኃይለ ሥላሴን ዙፋን አዳኑ፤ እዚህ ላይ ደግሞ ሌሎች ጥያቄዎችን ማንሣትና መልስ መስጠት ያስፈልግ ነበር፤ ግን አልሆነም፤ ጥያቄዎቹን አሁን እናንሣቸው፤ --

*1. ክብር ዘበኛ የቆመው ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ነው?*
*ለሕዝብ ነው? ለአገር ነው? የጦር ሠራዊትስ? የዓየር ኃይልስ?*
*2. የኢትዮጵያ ሕዝብስ ከማን ጋር ቆመ?*
*3. ከሁሉም በላይ አጼ ኃይለ ሥላሴስ ከዚህ ‹‹ክህደት›› ምን ተማሩ?*